

# ትንሣኤ



እመቤታችን ድንግል ማርያም የምሕረት ቃል ኪዳን እንደተቀበለች ።

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

## ማ ው ጫ

**አርእስት ፤** — **ገጽ**

ደብዳቤዎች ............ ፩
የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ............ ፪
ቃል ኪዳን ............ ፬
ቤተ ክርስቲያን በዓድዋ ............ ፭
ልማት በቤተ ክርስቲያን ............ ፯
ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብእ ............ ፱
የዕልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ............ ፲
ኃላፊነትን መዘንጋት ............ ፲፩
የግብርና በረከት ............ ፲፫
ቅዱስ ላሊበላ ............ ፲፭
የጋብቻ ኃላፊነት የነማን ነው? ............ ፲፯
ሰላም ............ ፲፯
ዜና ሊቃውንት ............ ፲፱
የደም ብዛት መከላከያ ............ ፳፩
የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ ............ ፳፫
ትምህርተ ግዕዝ ............ ፳፬

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፡

በመጀመሪያ የከበረ መንፈሳዊ ሰላምታዬን ሳቀርብ በትሕትና ነው ። ከዚህ ቀጥዬ ከቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እኔ ያልገባኝን መልስ ትሰጠኝ ዘንድ አቅርቤአለሁ ።

ከቤተ ክርስቲያን የማዕረግ ስሞች ውስጥ ከሥርዓተ ምንኩስና ጋር አባ ተብሎ ቅዱስ እስኪሜ የሚጨንለት ነው በመሆኑም ከቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ የብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ቲተር (የስም ማኅተም) አባ እገሌ ሊቀ ጳጳስ ዘ....የሚል መሆኑን ዘወትር የምንመለከተው ነው ከማዕርገ ምንኩስና በፊት ወይም በኋላ ሌላ የማዕረግ ስም የተሰጣቸው መነኮሳት አሉ ለምሳሌ መላከ ሰላም መ.ገነት መ.ኃይል ወ.ዘ.ተ. እነዚህ ሁሉ በቀጥታ በዚህ ስም ሲጠሩ ወይም ማኅተማቸው በዚህ ስም ሲቀረጽ አባ የሚለውን ስም አላስቀረውምን?

ይህ አሠራር በውጭ ሆኖ ለሚመለከታቸው ሕዝብ ምንኩስና እንዳላቸው በምን ሊያውቀው ይችላል? በአጠቃላይ ይህን አይነቱን ማዕረግ የተቀበለ መነኩሴ የምንኩስና ማዕረጉን እንዲሸፍን የሚያደርግ ሕግ አለ ማለት ነው ?

እንግዲህ እኔን እንደሚሰማኝ ሊቀ ሥልጣናት አባ እገሌ፣ መልአከ ኃይል አባ እገሌ ወ.ዘ.ተ. ተብሎ ማኅተም ቢቀረጽለት የሚያስቸግር ነገር አለን?
መልሱን በናፍቆት እጠባበቃለሁ ።

ጥበቡ መሠረት
ወሰጋ ሀገረ ስብከት
ነቀምቴ

፩ኛ. ያቀረቡት ጥያቄዎ እንደሚለው ለማንኛውም የቤተክርስቲያናችን የማዕረግ ስሞች ሁሉ ከሥርዓተ ምንኩስና በኋላ ከቅዱስ እስኬማው ጋር የሚሰጠው "አባ" የሚለው የማዕርገ ምንኩስና ስም ዐቢይና የበላይ ነው ሲሉ ጠይፋዋል ።

ርግጥ ነው አባ ማለት ትርጉሙ መንፈሳዊ አባት ሰይጣናትን በጸሎት ድል የሚነሣ ብርቱ ማለት በመሆኑ ጠያቂው እንዳሉትም ታላቅ ስም ነው ።

፪ኛ. ከፓትርያርክ ጀምሮ ሊቃነ ጳጳሳት ቲተር (የስም ማዕረግ) አባ እገሌ ሊቀ ጳጳስ ዘ....እየተባለ ሲጠራ ከምንኩስና በፊት ወይም በኋላ ሌላ የማዕረግ ስም የተሰጣቸው መነኮሳት ለምሳሌ መልዐከ ሰላም ፣መልአከ ገነት፣ መልዐከ ኃይል፣ ሊቀ ሥልጣናት እየተባሉ ሲጠሩ አባ የሚለውን የማዕረግ ስማቸውን ትተው ቲተር (የስም ማዓተም) አሠርተው በዚሁ ስም ብቻ አንዳንዶቹ ይጠራሉ ይህም አጠራር ማዕረገ ምንኩስና ያላቸውንና የሌላቸውን ለመለየት በቅርብ ለማያውቃቸው ያስቸግራል ሲሉ ጠይቅዋል ።

ነገሩ እስከዚህ አስቸጋሪ መስሎ አልታየንም ለማወቅ ከፈለጉ ግን መልዐከ ሰላም፣ መልዐከ ገነት፣ መልዐከ ኃይል የሚለው የማዕረግ ስም ከጐንደር መንግሥት ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የመጻሕፍት ትርጓሜ ለሚያውቁና ባለሕግ ለሆኑ ታላላቅ ሊቃውንት የሚሰጥ የሹመት ማዕርግ ሁኖ ቆይቶ ነበር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለሊቃውንት ብቻ ሳይሆን ለመነኮሳትም እንዲህ ያለው የሹመት ማዕረግ ያላቸውን መነኮሳት ይህ የሹመት ማዕረግ ስለሚሰጣቸው አባ የሚለውን ስም እንደያዙ በስሙ ይጠሩበታል አባ የሚለውን ማዕረግ በማህተመ ስማቸው የማያስቀርጹ ከሆነ ግን ከላይ የተጠቀሰው የሹመት ማዕረግ ሕጋውያን ለነበሩ ሊቃውንት የተሰጠ ስም በመሆኑ አባነታቸውን ሕዝቡ እንዲያውቅና እንዲረዳላቸው ይህንን ዐቢይ የሆነ የማዕረግ ስም በማህተማቸው ቢያስቀርፁ ጠያቂው እንዳሉት እኛም የዚሁ ደጋፊዎች ነን ።

## ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በየወሩ እየታተመ ለአንባብያን የሚቀርበው "ትንሣኤ መጽሔት" ከመጋቢት ወር ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ጀምሮ ዋጋው አንድ ብር የተደረገ መሆኑን ለደንበኞቻችን እንገልጻለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## የቤተ ክርስቲያን ሕይወት

ነፍስ የተለየው በ ድን መንቀሳቀስ እንደማይችል የወንጌል ቃል በምልአት የማይሰበክባት ቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ ናት ።

ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ሁኔታ አስቀድሞ በወንጌል የተነገረው የተስፋ ቃል" የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ አንተ ዓለት/ጴጥሮስ/ ነህ በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ" የሚል ሲሆን የቃሉ ትርጉም ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ትምህርት ትታነፃለች ማለት እንደነበር ተጽፎአል ።

ታዲያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በ ድን ወይም ግዑዝ ፆታ በሆነ አለት ላይ ሳይሆን ሕያዋን በሆኑ አዕማድና ሕይወት ባላቸው ዓለቶች ላይ ነው ። እነዚህም ዓለቶችና አዕማድ ወንጌልን የሚሰብኩ መምህራን ናቸው ።

በዘመናችን የሕዝበ ክርስቲያኑ ጥያቄ እነዚያ አዕማድና የማዕዘን ራሶች የሆኑ ሰባክያን የት ደረሱ? ቃሉን በትክክል የሚያስተምሩንን ሰዎች እንፈልጋለን'' የሚል ነው ። የጥያቄዎቹ መልስ ግን እስካሁን አልተሟላም ። የእግዚአብሔርን የመንግሥት ወንጌል የሚፈለገውን ያህል አሟልተው አስፍተው የሚያስተምሩ የበቁ የነቁ መምህራን ቁጥር አንሶአል የሚል ነው ።

ሆኖም በቅርቡ የሚታይ የብሩህ ተስፋ ነፀብራቅ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተ/ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ይህን ችግር በሚገባ ስላጤኑት ሁሉ ነገር ወደ ወንጌል ስብከት ሥራ እንዲያመዝን ተከታታይ መመሪያዎችን በመስጠታቸው ታላቅ የምሥራች አድርገን ተቀብለነዋል ። የቤተ ክርስቲያን ዓላማና ተግባር አልፋና ኦሜጋው ይኸው ነውና ።

ቀደም ብሎ የወንጌሉ ቃል የምሥራቹ በኩራት ከደረሰባቸው በኋላ እንደገና የቀዝቃዛ ሕይወት የታየባቸው ማለትም የወንጌል ስብከት ሥራቸውን ማስፋፋት ትተው በሰው ሠራሽ ልማድ መመራትን የመረጡ የሰባት አብያተ ክርስቲያናትን ጠቅላላ ሁኔታ የሚገልጥ አስገራሚ ራእይ ለዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ተገልጦለት ነበር ። እነዚያም አብያተ ክርስቲያናት የነበራባቸውን ጉድለት የሚጠቁም ትምህርት ተሰጥቶአቸው ሣለ አብዛኞቹ ተልዕኮውን ቸል ብለው በመገኘታቸው አንዳንዶቹ በመሬት ነውጥ ሌሎቹ በጦርነት ተደምስሰው በአሁኑ ጊዜ ዝክረ ስማቸው እንኳ ከገጸ ምድር ጠፍቶአል ።

አብያተ ክርስቲያናት የቱንም ያህል በወርቅና በዕንቁ አጌጠው ቢሠሩ የቱንም ያህል ስፋትና ውበት ቢኖራቸውም ምዕመናኑ በወንጌል ትምህርት ካልታነፁ በቀር ነገ አርጌውን በማደስ የሚጠግናቸው የጐደለውን አሟልቶ የተዛባውን አቃንቶ የሚንከባከባቸው እንዳያጡ ከአሁኑ ሊታሰብበት ይገባል ።

በአሁኑ ወቅት በተለይ ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ የልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት ምዕመናን ከከተማ እስከገጠር በሰበካ ጉባኤ እየተደራጁ አስተዋጽኦ በመክፈል ከሞላ ጐደል የካህናት ደመወዝ እየተሻሻለ በመምጣት ላይ ነው ከካህናቱ መካከል ግን ብዙዎቹ በዚሁ መጠን ዕውቀታቸውን እያሻሻሉ የወንጌልን ቃል አምልተውና አስፍተው ለማስተማር ምንም ያህል ዝንባሌ ካለማሳየታቸው የተነሣ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ገና እንደቀዘቀዘ ነው ። ለዚህም የመንፈስ ቅዝቃዜና ሙቀት መለኪያ የሚሆን ቃል በዮሐንስ ራእይ ተነግሮአል እርሱም" ኢ.ኮንከ ምውቀ አው ቆሪረ" ሞቃትም አይደለህ ፍጹም ቀዝቃዛም አይደለህ እስመ ማዕከላይ አንተ በመካከለኛነት ደረጃ ላይ ትገኛለህና ከሁለቱ አንዱን ቀዝቃዛነትን ወይም ሞቃትነትን ምረጥየሚል ነው ። እኛ ግን ከመካከለኛነቱም ደረጃ መድረሳችን እንኳ ያጠራጥራልና ልናሟላው የሚገባን ገና ብዙ ተግባር አለን ።

የእግዚአብሔር መንፈስ በነቢዩ ሆሤዕ አድሮ ሲናገር "ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል አንተም ከአሁኑ ሕጌን እረስተሃል እኔም ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ ክብራቸውንም ወደ ነውር እለውጠዋለሁ፣ሕጌንና ሥርዓቱን ለማወቅ የምትችልበትን ትምህርት ጠልተሃልና እኔም ደግሞ ካህን እንድትሆነኝ አልፈልግም ወካህንኒ ከመ ሕዝብ ካህኑም ብሎ ብሎ እንደ ሕዝብ ሆነ ስለዚህም በአካሂዳቸው ሁሉ እበቀላቸዋለሁ ወአስተዳድቆሙ እርስበርሳቸውም እየተጣሉ እንዲጓሸሙ አደርጋለሁ" ማለቱ ይታወሳል ።ሆሴ ፬ ፣ ፩-፲



ይህ ትንቢት በእኛ ላይ አልተፈጸመም ብለን ልንዋሽ አንችልም ። ከንጹሕ ስንዴ ውስጥ እንክርዳድ እንደማይታጣ የአንዳንድ ደብር ካህናትም ሕይወት ልክ በዚህ ዓይነት መገኘቱን የሚገልጥ ማስረጃ አለና ነው ።

መፍትሔውስ?ቢባል የወንጌል ቃል በምልአት እንዲሰበክ ከማድረግ የተሻለ ሌላ አማራጭ ነገር የለም ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ሰላም ለመጠበቅና ኅብረት፣የጠነከረ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት እንዲኖራት ለማድረግ በየቢሮዎችዋ ዘብ ጠባቂዎችን ማቆም ሳይሆን ዋና መሣሪያዋ"ንሥኡ ሰይፈ ዘመንፈስ ቅዱስ ዘውእቱ ቃለ እግዚአብሔር "የመንፈስን ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎ የተጻፈውን እንዲሰብክ ማድረግ ብቻ ነው ።ኤፌ ም. ፮ቁ.፲፯

በወንጌል ትምህርት ያልታሸ ክርስቲያናዊ ሕይወትና ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኘው የደህንነት ጸጋ ዘይት ያልለሰለሰ ልብ በቅጣትና በማስፈራት ብቻ ይቃናል ማለት ዘበት ሆኖ መቅረቱ ብዙ ጊዜ ተፈትኖ ያበቃ ጉዳይ ነው ።

በመሠረቱም መታወቅ ያለበት አንድ ታላቅ ቁም ነገር ማናቸውንም ትምህርት አስተምሮ አንድን ሰው ከተወሠነ ደረጃ ለማድረስ በቀላሉ የጥቂት ዓመታት ጊዜ ሊበቃ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ሲችል የሠለጠነ አንድ ጥሩ ሰባኬ ወንጌል ለማግኘት ግን የብዙ ዓመታት ልምድ የሚጠይቅ መሆኑን ልናስታውስ ይገባል ። ስለዚህም ካሉን ካህናት መካከል በተለይ ለወንጌል ስብከት ሥራ መልካም ፈቃድና ዝንባሌ ያላቸውን በመብራት እየፈለጉ በማሰባሰብና በጥንቃቄ በመምረጥ ማሠልጠን የሚቻልበትንም ዘዴ መፈለግ ያሻል ።

ለዚህም የምናቀርበው ጥቆማ ከዚህ በፊት በቀድሞው መንፈሳዊ ኮሌጅ ያስተምሩ የነበሩ ታላቅ ምሁር አቅርበውት የነበረ አንድ ዕቅድ "አሁን በሥራ ላይ ላሉት የወንጌል ስብከት መምህራን ተጨማሪ የትምህርት ፕሮግራም አዘጋጅቶ በምልአትና በስፋት ጥሩ ተጨማሪ ትምህርት እንዲያገኙ ያስፈልጋል" የሚል ነበር ። ይህ ዓይነቱ የተቀደሰ ዕቅድ ዛሬም እንደገና ሊታወስና ተግባራዊ መሆን የሚችልበት ዘዴ እንዲፈለግለት ከማሰብ አንቆጠብም ። እምና በወቅቱ በአዲስነቱ የተሻለና የማይበርድ ሥለት የነበረው መጥረቢያ ዘንድሮ ሞረድ ሊያስፈልገው እንደሚችል የወንጌል መምህራንም በልዩ ልዩ የተሐድሶ ትምህርት እየተሞረዱ እንደገና ይሣሉ ዘንድ ያስፈልጋል ይህ ካልሆነ ግን በድልዱም ማረሻ አርሶ የቱንም ያህል ግዳጅ መፈጸምና ብዙ ማምረት አይቻልም ።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እያበበች እንደበትረ አሮን ፍሬ የምላበት ሆና እንድትገኝ ወይም በፈሳሽ ወንዝ ዳር ተተክላ በየጊዜው ፍሬ እንደምትሰጥ ልምላሜዋም እንደማይጠወልግ ዕፀ ሕይወት (ተክል) ሆና እንድትኖር እንደመስኖ ውኃ የሚያረሰርሳትን የቃለ ወንጌል አሸንዳ በስፋት መክፈት ያስፈልጋል እንላለን ። ያለንበት ጊዜ ካለፈው በተሻለ ሕይወት ሕዝበ ክርስቲያኑ የውኃ ምንጮችን እንደተጠማ የእግዚአብሔርን ቃል የሚናፍቅና ወዲህም ደግሞ የሰባክያነ ወንጌልን ችሎታ በቀላሉ መገመት የሚቻልበት ዘመን ነውና።

ስለዚህም የወንጌል ስብከቱ ሥራ እንደወይፈን እርሻ ተልኮስኩሶ እንዳይቀርና የማስተማር ዘዴያችንም ከዘመኑ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም ዳባ ና ካባ እንዳይሆን ወይም በኮምፒይተር ዘመን በባቁላና በጠጠር እንደማስላት እንዳይቆጠርብን የምናሠልፋቸው ሰባክያነ ወንጌል ሞገስና ጸጋ ባለው ጣዕመ ልሣን ተናግረው የምዕመናንን ሕይወት የሚያረኩበት ብቃትና ዝግጅት እንዲኖራቸው አዲስ መርሐ ግብር መንደፍ ከሚያስፈልግበት ዐረፍተ ዘመን ላይ መድረሳችንን እንርሳ ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቃል ኪዳን

በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊው ዓላማ ሁለት የተለያዩ ወገኖች /ክፍሎች በመካከላቸው ቋሚ ሁኖ ሊኖር የሚችል ግንኙነት የሚያደርጉት ስምምነት ወይም ውል ቃል ኪዳን ተብሎ ሊተረጐም ይችላል ።

ቃል ኪዳን በተለይ በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል የተጠበቀ ሁኖ ሲገኝ ነው በሥራ ተተረጐመ የሚባለው ጥቅምም ሊኖረው የሚችለው ይህ ሲሆን ነው እስዚያ ግን ፍሬ ቢስ ሁኖ ጥቅም ሣይኖረው ይቀራል ። በሰዎች መካከል የሚደረገው ቃል ኪዳን በመሰረቱ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን ግዴታእ ያስከተለ በየዘመኑ ለተከታታዩ ትውልድ ሁሉ በሥራ ተገልጦ ይታያል ለማንኛውም ጉዳይ ውል ያስፈልገዋል ዳኛም ቢ. ፈርድ ሽማግሌም ለማስታረቅ ቢመከር ገመጀመሪያ ለነገሩ መነሻ የሆነውን የነገሩን ውል ማግኘትና መስማት መያዝም ያስፈልጋል ። ምክንያቱም "ነገር ከስሩ ውሐ ከጥሩ" እንደሚባለው ነውና የመጀመሪያው ውል ካልተገኘ ለመፍረድም ሆነ ለማስታረቅ መግቢያ ለማግኘት አይቻልም ውል ካለ ግን በውሉ መሠረት እየተረዱ ማንኛውንም ነገር ለመፈጸም ይመቻልና ነው ።

ነገር ግን ይሕ ቃል ኪዳን በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የተጠበቀ መሆን አለበት ከሁለቱ ወገን አንዱ ቃል ኪዳኑን ቢያፈርስ ሌላው ወገን ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ግዳጅ የለበትም ቃል ኪዳን አፍራሹን ክፍል በሽማግሌም ሆነ በዳኛ ሊያስቀጣ ይችላል ። ይሕ በሰዎች መካከል የሚደረግ ቃል ኪዳን ሊፈርስም ላይፈርስም ሊፈጸምም ላይፈጸምም ሊጠበቅም ላይጠበቅም ይችላል በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የተደረገው ቃልኪዳን ግን ሊፈርስ የማይችል ሰው ሰራሽ በመሆን ዛሬ ተነግሮ ነገ ሊጠፋ የሚችል አይደለም።ቃል ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከልም ብዙ ጊዜ እንደተደረገ በቅዱስ መጽሐፍ በብዙ ምዕራፎች ተጽፎ እናገኛለን በዚህም መሠረት በእግዚአብሔርና በመጀመሪያው ሰው በአባታችን አዳም መካከል የነበረው ግንኙነት ከዚሕ የተለየ እንዳልነበረ እንረዳለን ለአዳም አባታችን ማንኛውንም ነፃነት ለመወሰን የሚያስችል የውዴታም ሆነ የግዴታ ያለበት ነፃነት ተሰጥቶት ነበር ። ነገር ግን የነፃ ፈቃድ መለኪያ የሆነውን ቃል ኪዳን በተግባር ሊፈጽመው/ሊገልጠው/ባለመቻሉ መርገምና ፍዳ ሊደርስበት በቅቶአል።እግዚአብሔር ግን አባታችን አዳምን ይሕን አልፈጸመም ብሎ በመርገሙና በፍዳው ትቶት አልቀረም በበደሉም የተነሣ ስለአዘነለትና ስለተፀፀተ በሥጋ በመገለጽ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀል ላይ ሞቶ የበደሉን ዕዳ በደሙ ለመካስ ፈቃዱ ሆነ በዚህም የምሕረት ቃል ኪዳኑ የተፈጸመ መሆኑን ቅዱሳት መጽሐፍት ያረጋግጡልናል ።

እግዚአብሔር አምላክም በመጀመሪያ ዓለም ስለሠራው ከባድ ኃጢአትና ስለሐጢአቱም ብዛት በጥፋት ውኃ በኮነነበት ጊዜ ለኖህ በተናገረው ቃል ኪዳን መሠረት እሱንና ቤተሰቦችን ከጥፋት ውኃ ለማዳን በጠቅላላው እርሱንና ቤተሰቦቹን ብቻ ሳይሆን በመርከቡዋ ውስጥ የነበሩትን ሕያው ነፍሣት ሁሉ አዳነ የጥፋት ውኃ በጐደለና በደረቀ ጊዜ እግዚአብሔር ለኖህ ቃል ኪዳን አድርጐለታል ይኸም የምሕረት ቃል ኪዳን ምልክት ሰባት ቀለማት ያሉት በሰማይ ላይ በደመና ተዘርግቶ የሚታየውን ቀስተ ደመና ነበር ይሕም በእኔና በምድር ላይ ሥጋን በለበሰ ሁሉም መካከል የምሕረት ኪዳን ምልክት ስለሆነ ዓለምን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አላጠፋም ሲል ለኖህ ቃል ኪዳን ሰጥቶታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል የተደረገ ቃል ኪዳን ነው እርሱም አብርሃም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠለትና እኔ እግዚአብሔር ነኝ በፊቴ ተመላለስ ፍጹምም ሁን ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል አደርግአለሁ እጅግም አበዛሐለሁ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሐለሁና እጅግም አበዛሐለሁ ዘርህንም ከሰማይ ከዋክብትና ከባሕር አሸዋ አበዛዋለሁ ሲል ቃል ኪዳን ሰጥቶታል ዘፍጥ.፲፯ ቁ ፮-

ታዲያ ይሕ ዓይነቱ ቃል ኪዳን ለኖህና ለአብርሃም ብቻ የተሰጠ ሣይሆን ለእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረው ሙሴም አምላኩን እባክህ እንደምረትሕ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በልበማለት በማለደ ጊዜ እንደቃልህ ይቅር እላለሁ ከመረጥኩት ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ ያለውን ቃሉን እንዳፀና ልንረዳ እንችላለን ።

እግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ የኪዳኑ ምልክት ታቦት ነበር በዚህም መሠረት እግዚአብሔር ለብዙዎቹ አባቶችና ቅዱሳን ቃል ኪዳን እንደሰጠ ጠቅሰናል ከአባቶችና ከቅዱሳን በይበልጥ ለአባቶችና ለቅዱሳን እናታቸው ለሆነችው ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም እናታችን እግዚአብሔር እጅግ ከፍ ያለ ቃል ኪዳን ሰጥቷታል ይኸውም ለተቸገሩት ሁሉ የምሕረት አማላጅ እንድትሆን ነው በብሉይ ኪዳን የነበሩት ሰዎች ቃል ኪዳን እንደተቀበሉ ተናግረናል ይሁን እንጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ተወልዶ የዓለምን ኃጢአት በሞቱ እስከአስተሰረየ ድረስ ግን የዓለም ደኅንነት ሊገኝ አልቻለም ነበር ከዚያ ወዲህ ግን ክርስቶስን የወለደችው ቅድስት ድንግል ማርያም በተቀበለችው ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር በመጥፎ ሥራቸው የተለዩ ሁሉን ስሐ ገብተው እርሷን ቢለምኑ አማላጅነት ከልጅዋ የተሰጣት ስለሆነ ሰዎችና እግዚአብሔርን በማማለድ ታስታርቃለች እውነተኛዋ የኖህ ቀስተ ደመና የእስራኤል ታቦት እርሷ ናትና

ይህንን የተረዱ ሊቃውንትም "የማህፀንዋ ፍሬ ዓለምን አዳነ በአንችም ምክንያት ዓለም ዳነ ሰላምም ሆነ" እያሉ አመስግነዋታል ።ቅድስት ድንግል ማርያም በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት ታማልደናለች ስንል የልጅዋን የክርስቶስን አዳኝነት፣መሐሪነት፣ይቅር ባይነት በመዘንጋት መሆን የለበትም እርስዋ ይሕንን ፀጋና ሞገስ ለማግኘት የቻለችው መድኃኒታችንን ክርስቶስን በመውለድዋ ነውና እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነቷን ከአመንና በእርሷ ከተማፀን እርሷን ማፍቀር ያስፈልጋል በመጀመሪያ ግን የክርስቶስን መሐሪነት አዳኝ መሆኑን ማመን ይጠቅማል በመጽሐፈ ተአምሯ በሰፊው ተጽፎ እንደምናገኘው በቅድስት ድንግል ማርያም በስምዋ ወደፈጣሪው የተማፀነ ቃል ኪዳንዋን የጠበቀ ምሕረትን እንደሚያገኝ ነው ። ነቢይን በነቢዩ ስም የተቀበለ የነቢዩን ዋጋ ይቀበላል ጻድቁንም በጻድቁ ስም የተቀበለ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል ማንም ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙሩ ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ማቴ ም.፲ ቁ.፵፩

ይልቁንም ድንግል ማርያም በተሰጣት ቃል ኪዳን የምታማልድ ምሕረትን ከልጅዋ የምትለምን ከርሷ በተወለደው በክርስቶስ አምነው ለሚማፀኑአት ስለ ኃጢአታቸውም ንስሐ ገብተው ሐጢአታቸው እንዲሰረይላቸው ነው

ስለዚህ ማንም ሰው ከእርሷ በተወለደው በክርስቶስ አምኖ ለእምነቱም መግለጫ የሚሆነውን መልካም ሥራ ሠርቶ የድንግል ማርያምን ስም በመጥራትና በስምዋ በመዘከር እንደሚድን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ያስረዳሉ. የክርስቶስን ፍጹም አዳኝነት አምነን መልካም ሥንሠራ ድንግል ማርያምም የደኅንነት መገኛ መሆኗን እናምናለንና ። እግዚአብሔር ለዓለም የሰጠው ቃል ኪዳን በእርሷ ተፈጽሟልና ።

እንግዲህ ቃል ኪዳናችን በቃል ኪዳን ሰጭውና ቃል ኪዳን ከተሰጠችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር እናድርግ "ኪዳነ ተከየድኩ ምስለ ሕሩያንየ" ከመረጥኳቸው ወዳጆች ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ ተብሎ ተጽፎአልና ።

ስለዚህ እመቤታችን ድንግል ማርያም የምሕረት ቃል ኪዳን የተቀበለችው የካቲት ፲፮ ቀን በመሆኑ ይህም በዓል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ ሲከበር ይኖራል ።

ፍሥሐ ባንተ



# ቤተክርስቲያን በዓድዋ

የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያነብና የሚመረምር ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለነፃነት ፡ ስለ ጥንታዊ ባሕልና ስለቅርሳቅርስ መጠበቅ ከፍ ያለ ተጋድሎ ያደረገች መሆኗን በቀላሉ መገንዘብ ይችላል ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በእምነት በኩል ቀደም ሲል ሕገ ኦሪትን ኋላም ከ፩ኛው ምእት ዓመት ጀምሮ የክርስትና ሃይማኖትን ተቀብላ የኖረች በመሆኗንቃትና ብቃት አግኝታ ነፃነቷን ሳታስደፍር ለብዙ ዘመናት ኖራለች ለሦስት ሺህ ዓመት ያህል የማንም የውጭ እጅ ጣልቃ ሳይገባባት ራሷን በራሷ እየመራች በአፍሪካ አህጉር የነፃነት አንጋፋ ሀገር ሆና በመቆየቷም የዓለም ሕዝብ ሲያደንቃት ይኖራል ።

ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን እንደ ቅርጫ ሥጋ ሲከፋፈሉ የነፃነት ደሴት ሆና የቆየች ዝነኛ ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ ነበረች ። ይህም በጸጋ ብቻ የተገኘ ሳይሆን ለነፃነቷ መጠበቅ ምክንያቶች የሆኑ ብዙ ቁም ነገሮች አሉ ። ከነዚህም አንደኛው ሕዝቡ ስለሀገሩ ያለው ታማኝነት ሲሆን 2ኛው ደግሞ ሀገሪቱ ቀደም ሲል የክርስትናእምነትን ስለተቀበለች በመጽሐፍ ቅዱስ እያሳበቡ ሀገርን የሚወሩ ቅኝ ገዥዎች መግቢያ ቀዳዳ በማጣታቸው ነው።በልዩ ልዩ ዘዴ እያሳበቡ ለመግባት ቢሞክሩም በሕዝቡ ብርታት እየተባረሩ በመመለሳቸውና ተቀባይም ባለማግኘታቸው ዓላማቸው ሊሳካላቸው አልቻለም 3ኛውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስለነፃነት ጥቅም ከማስተማሯም በላይ የሃይማኖት ነፃነት ሊኖር የሚችለው የሀገር ክብርና ነፃነት ሲኖር መሆኑን በማስረዳት ሕዝቡ ለሀገርና ለሃይማኖት መስዋዕት መሆን እንዳለበት የቤተ ክርስቲያን መምህራን ትምህርት ስለሚሰጡ ጠላት በመጣ ቁጥር በቆራጥ መንፈስ እየተዋጋ መብቱንና ክብሩን ስለሚያስጠብቅና የሀገሩንም ድንበር ስለሚያስከብር ነው ። ስለሀገር ፍቅርና ስለመስዋዕትነት ማስተማር ብቻ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ማለት ጳጳሳቱ ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ሊቃውንቱም ጭምር ጦርነት በተነሣ ቁጥር ከጀግኖች አባቶቻችን ጐን በመሰለፍ ራሳቸው እየተዋጉና እያዋጉ ለሀገራቸውና ለነፃነታቸው ለወገናቸውም ራሳቸውን መስዋዕት እያደረጉ ጭምር ነው ። ለዚህም የዛሬ 87 ዓመት በዓድዋ ላይ የተፈጸመው የጀግንነት ታሪክና የተገኘው ወርቃማ ድል እውነተኛ ምስክር ነው ።

የኢጣልያ ፋሺስት በጊዜው በነበረው የመሣሪያ ክምችት በኃይሉ፣በሀብቱና በሥልጣኔው ጭምር ተመክቶ ይህችን ውብና ነፃ ሀገር ለመውረርና ቅኝ ግዛት ለማድረግ ባሕር ተሻግሮ የብስ ረግጦ በመጣ ጊዜ ሀገሪቱን ለመያዝ ምክንያት ባይኖረውም ለጊዜው የውጫሌን ውል 17ኛውን አንቀጽ መንሥኤ በማድረግ እንደ ጅብ "አታደፍርሺብኝ" የሚል አይነት ሀሳብ ፈጥሮ ቢመጣም ኢትዮጵያ "ሳታመካኝ ብላኝ" ብላ ዝም አላለችም።በዘመኑ የነበሩት የሀገሪቱ

ወደ ገጽ ፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ባለፈው እትማችን በወሎ ሀገረ ስብከት በደሴ ከተማ የገነተ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ስለአደረጉትናስለሚያደርጉት የልማት እንቅስቃሴ መግለጣችን የሚታወስ ነው በዛሬው እትማችን ደግሞ በጋሞ ጐፋ ሀ/ስብከት በጋሞ አውራጃ በጩንቻ ከተማ ካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት ቅጽረ ግቢ ስለሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ እንገልጻለን ።

የጩንቻ ከተማ መድኃኔ ዓለም ካህናት ማሠልጠኛ ከተቋቋመ ከ፳ ት ዓመታት በላይ ሲሆነው በርከት ያሉ ካህናትን እያሠለጠነ አስመርቋል አሁንም በርከት ያሉ ካህናት በመሠልጠን ላይ ይገኛሉ በትምህርት ቤቱ ለሚሰለጥኑት ካህናትም ከቀለም ትምህርት ጋር የተግባረዕድና የሌላም የልማት ትምህርት ይሰጣቸዋል በዚሁ ትምህርት ቤት ቅጽረ ግቢ የተቋቋመ ተግባረዕድ ስላለ ካህናቱም ይሳተፉበታል ።

ተግባረ ዕዱ የተቋቋመው ትምህርት ቤቱ እንደተቋቋመ ለካህናቱ ማሠልጠኛ እንዲሆን ታስቦ ሲሆን የተቋቋመበት ዘመን 1971 ፣ ዓ.ም. ነው ነገር ግን አስፈላጊው መሣሪያ ተሟልቶ ባለመቅረቡ ተግባረ ዕዱ እንደተቋቋመ ሥራውን አሟልቶ ተፈላጊውን ሥራ ለማከናወን ብዙ መሰናክል ገጥሞት እንደነበር ታውቋል ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው ከላይ እንደተጠቀሰው በ1971 ዓ.ም. ቢሆንም ተፈላጊዎች የሆኑት መሣሪያዎች ተሟልተውለት ሥራውን በሚገባ መሥራት የጀመረው ከ1973 ዓ.ም. ወዲህ ነው ።

ይህ ተግባረ ዕድ ከተጠቀሰው ዘመን ወዲህ የእንጨት መሳሪያዎችን መሮዎችን ና የመሳሰሉትንም ዕቃዎች አሟልቶ ሥራውን በሚገባ እየሠራ አሁን ከሚገኝበት ደረጃ መድረሱን ተረድተናል በትምህርት ቤቱ ቅጽረ ግቢ የሚገኘው ይህ የተግባረ ዕድ ክፍል ሥራውን የሚያካሂደው በሦስት ታላላቅ ክፍሎች በመከፈል ሲሆን እነርሱም ፣

አንደኛ የቅርቃሃ

ሁለተኛ የእንጨት

ሦስተኛ የሽመና ሥራ ናቸው ።

በቅርቃሃው ሥራ ክፍል

ኩርሲዎች /ድጋፍ የሌላቸው ወንበሮች/ መቀመጫዎች

ባለቀንድና በለድጋፍ ወንበሮች

ጠረጴዛዎች

የፎቴ ወንበሮች

የፍራፍሬ ማቅረቢያዎች ዝርግ ሳህኖች

ዘንቢሎችና ባለመክደኛ ሳህኖች

የመጽሐፍ መደርደሪያዎች

የአምፑል መያዣዎች

መሶብና አገልግል ቅርጫትና የመሳሰሉትም ተመልካችን በሚማርኩ አኳኋን ይሠራሉ፡-

በእንጨት ክፍሉ ወንበር፣ጠረጴዛ፣ቁም ሳጥን፣የልብስማስቀመጫ ሳጥን፣የመጽሐፍ መደርደሪያ፣በየአይነቱለንብ እርባታ የሚውሉ ቀፎዎችና የመሳሰሉትም እየተሠሩ ይቀርባሉ ።

በሽመና ክፍሉ ደግሞ ቡሉኮ ፣ጋቢ ጥበብ ነጠላ ፣ቀሚስና ኩታ ለኮትና ለሱሪ ለመጋረጃ ለፎቴ የሚያገለግሉ ልብሶች ለመሠልጠን በተሰበሰቡት ካህናት እየተሠሩ ለሽያጭ ይቀርባሉ በተጨማሪም በተፈጥሮ ወይም በልዩ ልዩ አደጋ ለተጐዱ አካለ ስንኩላን ምርኩዞች ለበሽተኞቹ በሚያመችሁኔታ እየተዘጋጁለተጠቃሚዎቹ ይቀርባሉ፣ከዚህምሌላ ከብረት ጋር የተያያዙ የቆዳና የጐማ ጫማዎች ይሠራሉ ።

ለዚሁ ተግባረዕድ ሐላፊ የሆኑትን መሪጌታ ገብረ መድህንን ስለሥራው አንዳንድ ጥያቄዎችን አቅርበንላቸው ማብራሪያ ሰጥተውናል ።

ጥያቄ፡- በዚህ ተግባረዕድ ክፍል ተመድበው የሚሠሩ ሠራተኞች ቁጥር ስንት ይሆናል?

መልስ ፡- ተግባረ ዕዱ የተቋቋመው ካህናቱን ለማሠልጠን ስለሆነ ከየአውራጃውና ከየወረዳው የተሰበሰቡ ካህናት እየተማሩ የሚሠለጥኑበት ስለሆነ ከእኔ በስተቀር ሌላ ቀዋሚ መደበኛ ሠራተኛ የለም ነገር ግን ለመሠልጠን የሚሠበሰቡት ካህናት ሁሉ በፕሮግራም ከተግባረ ዕዱ ይሳተፋሉ?

ጥያቄ፡- በሽመናው ክፍል ውስጥ ብዙ ልብሶች በውጥን ላይ ይታያሉ የተጀመሩት ልብሶች በስንት ቀን ሊያልቁ ይችላሉ ?

መልስ ፡- ቀዋሚዎች ሠራተኞች ስለሌሉ ሠልጣኞቹ ካህናት በፕሮግራም ነው የሚሠሯቸው ስለዚህ እንደልብሱ ዓይነት ነው በአንድ ወር የሚያልቅ አለ ከዚያም በላይ የሚጨምር ይኖራል ።

ጥያቄ ፡- የአንዱ ልብስ ዋጋ ምን ያህል ይሆናል ?


መልስ፡- የእያንዳንዱ ልብስዋጋ የተለያየ ነው ለምሳሌ ቡሉኮ 50-80 ብር ሲሸጥ ጋቢው ከ20 - 30 ኩታና ቀሚስ 25 - 30 ነጠላ እስከ 15 ብር የሱሪውና የኮቱ ልብስ 20 - 25 ይሸጣል

ጥያቄ፡- በሚደረገው የተግባረዕድ እንቅስቃሴ ላይ ምን ዓይነት ችግር አለባችሁ? ችግሩስ በምን ዓይነት መንገድ ሊቃለል ይችል ይመስልዎታል?

መልስ፡-በጥሬ ዕቃው አቀራረብ ላይ ከፍያለ ችግር አለብን ሥራው ገና ያልደረጀ እንደመሆኑ መጠን ተፈላጊዎች የሆኑትን ዕቃዎች ገዝተን የምናቀርብበት በርከት ያለ ገንዘብ የለንም

አሁንም የምናደርገውን የልማት እንቅስቃሴ የምናካሂደው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በምታደርግልን እርዳታ ነው ወደፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ይህንን ችግራችን ተመልክቶ እርዳታ ቢያደርግልን ተፈላጊውን ዕቃ በወቅቱ በማቅረብ ከፍተኛ ውጤት ለቤተ ክርስቲያናችን ለማቅረብ እንችላለን

ጥያቄ፡- ስለዚሁ ተግባረ ዕድና ስለሌላም የልማት ተግባር የታቀደ ዘዴ እንዳለ ቢያስረዱን?



በጩንቻ የካህናት ማሰልጠኛ ውስጥ የተግባረ ዕድ መምህር ገ/ መድኅን

መልስ፡- በአካባቢያችን ባዶ የሆነ ቦታ ስለአለ ለልማት ከፍ ያለ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንገኛለን አሁንም በመጠኑ ተልባ ዘርተን ውጤቱን በመጠባበቅላይ ነን ከዚህ ሌላ የንብ እርባታ ለመጀመር ቀፎዎችን በዘመናዊ እቅድ በመሥራት ላይ እንገኛለን ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ችግሩ የገንዘብ እጥረት ጉዳይ ነው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደምታደርግልን ከፍተኛ እርዳታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና የክርስስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያም የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ አድርጐልን ወደፊት ያቀድነውንዓላማ ከግቡ እንደምናደርሰው ተስፋ እናደርጋለን ።

የጋሞ ጐፋ ሀ/ስብከት ካህናት በትምህርት በልማትና በተግባረዕድ ንቃት እንዲኖራቸው በየጊዜው ያልተቆጠበ እርዳታ ስለምታደርግ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዚህ አጋጣሚ ልትመሰገን ይገባታል በማለት መሪጌታ ገብረ መድኅን ዓለምቦ የተግባረ ዕዱ ማሠልጠኛ ሐላፊ አሳባቸውን ደምድመዋል ።

በጋሞ አውራጃ በጩንቻ ከተማ ካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ቅጽረ ግቢ የሚገኘው የተግባረ ዕድ ክፍል በቤተ ክርስቲያን በኩል ከፍ ያለ ተስፋ የሚጣልበት ስለሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትናክርስቲያናዊ ተራድ መምሪያም የእርዳታ እጁን መዘርጋት ያለበት እንደዚህ ላለው የተግባረዕድና የልማት እንቅስቃሴ ይመስለናል የጋሞ ጐፋ ሀ/ ስብከት ጽ/ቤትም ለተግባረዕዱ የጥሬ ዕቃዎች በተፋጠነ መንገድ የሚቀርቡበትን ና የተሠሩትም የተግባረዕድ ውጤቶች ለሽያጭ የሚቀርቡበትን ቦታ የማዘጋጀት ሐላፊነት አለበት ።

ቄ/ልሣነ ወርቅ በዛብህ

# የግብርና ሥራ ...

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ዓቴን ጠብቅ ይህንስታደርግ"ለአባቶችህ በማለላቸው ምድር የሆድህን ፍሬ የመሬትህንም ፍሬ ፣ እህልህን ፣ ወይንህንም ፣ ዘይትህንም የከብትህንም ብዛት የበግህንም መንጋ ይባርካል በሰውህና በከብትህም ዘንድ ወንድም ቢሆን ወይም ሴት ብትሆን መካን አይሆንብህም እግዚአብሔር ሕማምን ሁሉ ካንተ ያርቃል ክፉው በሽታ ሁሉ በአንተ ላይ አያደርስብህም ዘጸ. 7ቁ. 13-15" ብሎአል ።

ይህ አምላካዊ መመሪያ የሚያመለክተን የሰው ልጅ የሚሰጠውን መምሪያ ተግባራዊ ሲያደርግ ከብቶች ሲራቡ ጤናቸው ተጠብቆ የእርሻ በረከት ያለችግር ሊስፋፉ እንደሚችል ነው ።

አዎ ከብቶች በጤናቸው ሲጠበቁ ሲረቡና ሲራቡ የግብርና በረከት ሊስፋፋ እንደሚችል እናምናለን ፣ የግብርና በረከት ሲስፋፋ የእራሹ ጤና ሲሟላም ጤናማ ዜጋ እየበዛ የሀገር ደህንነት ይጠበቃል ማለት ነው ።

ስለዚህ ከላይ ከባለሙያዎች በተገለጸው መሠረት ከጠንቀኛ ዝንብና ዝንብን ሊያመጡ ከሚችሉ ጉድለቶች መጠንቀቅና ባለሙያዎች በተደጋጋሚ የሚሰጡትን ትምህርታዊ መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ።

የግብርና ሚኒስቴር መመሪያ ተግባራዊ ሲሆን የግብርና በረከት በአገራችን የበለጠ ተትረፍርፎ ለዓለም እንዲዳረስ (ያበቃናል) ይረዳናል ።

በለጠ አበበ





www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያን በአድዋ

ከገጽ ፭ የዞረ

መሪ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ቆራጥ የሆኑ ጀግኖቻቸውን አስልፈው ወደ አድዋ በአመሩበት ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እጅዋን አጣምራ አልተመለከተችም ። የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ታቦትና መስቀል ይዘው ከጀግኖች አባቶች ጋር በመሰለፍ ስለነፃነታቸው ተጋድለዋል ።

ስለ ኢጣሊያኖች አመጣጥ የዓለም ታሪክ እንደሚያስረዳን ጣሊያኖች ባሕር ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ምድር ከገቡ በኋላ ሐማሴንን ወደኋላቸው ትተው መረብን ተሻግረው ወደ ማኅል ኢትዮጵያ ለመግባት ወደመካከለኛው ትግራይ ለመግባት እየተሹለከለኩ በስተ አድዋ አፋዛኝና በሌላም በኩል ብቅብቅ ማለት ሲጀምሩ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ይህንኑ ለአፄ ምኒልክ ባስታወቋቸው ጊዜ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ም ወዲያው የጦር አለቆቻቸውን ሠራዊቱን አስከትለው ከሸዋ ወደ ትግራይ እንደገሠገሡ ተጽፏል ።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በአድዋ ጦር ግንባር ከመሰለፋቸው ቀደም ሲል ከጠላት ወገን አንድ ክፍል የሚሆነው ጦር በአንድ ፊታውራሪ ተመቶ ቆይቷል ። ከዚህ በኋላ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም የጣሊያን ሰልፍ ወደ አፄ ምኒልክ አስፍስፎ መጥቶ አድዋ ላይ ገጥሞ ከተዋጋቸው በኋላ አፄ ምኒልክ ጣሊያኖችን ድል ነሥተው ምርኮውንም ጥርግርግ አድርገው ይዘው ወደዋና ከተማቸው ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን ይኸው የዓለም ታሪክ በአጭር አገላለጥ መዝግቦታል ። ይህ ታሪክ በጊዜው የሀገሪቱ መሪ ሆነው የድሉ ባለቤት በነበሩት በዓፄ ምኒልክ ስም ተጠቃሎ በአጭሩ የተቀመረ ይሁን እንጂ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ይህን ታላቅ የጀግንነት ውጤት የተቀዳጁትና ለሀገሪቱም በመላው ዓለም ዝናን ያተረፉላት ይህን የአድዋን ድል ለማግኘት የቻሉት በእምነታቸው የጸኑ በሀገር ፍቅር የተቃጠሉና በጀግንነት ስሜት የበሰሉ መንፈሰ ቆራጥ ሕዝቦች በጦርነቱ በመሰለፋቸውና መስዋዕት በመሆናቸው ነው ። ከመካከላቸውም ስለሀገርና ስለወገን ክብር መሞት ሰማዕትነት መሆኑን የሚያስረዱ እውነተኞች ካህናት በመኖራቸው ሠራዊቱ በካህናቱ ምክር እየተጠቀመ ያላንዳች ማመንታት በቆራጥነት ስለተዋጋ ነው ። ናስማስር፡ውኸ'ርግራሲናደርና ወጨፎ እንዲሁ ምጉራዴና፡ጦር መጥረቢያና፡ዱላ ጭምር ይዞ የዘመተው ይህ ቆራጥ ሠራዊት ዘመናዊ ጦር መሣሪያ ታጥቆ በከባድ ኃይል የመጣውን ጠላት ግንባር ለግንባር ገጥሞ እንደ መከር እህል እያጨደ እየወቃ በጣለው ጊዜ የጠላት ጦር መግቢያ ቀዳዳ ከማጣቱም በላይ ድል በመመታቱ በአድዋ ላይ የበራው የድል ችቦ የነፃነት ጮራ ሆኖ እስከ ዛሬ በመላው አፍሪካ እያበራ ይኖራል ።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለዚህ ታላቅ ድል ከመብቃታቸው በፊት ወደጦርነቱ ለመዝመት ሲነሡ ለሕዝባቸው ያስተላለፉት ጥሪ ያገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ሀገርህን የሚወር ክብርህንና ነፃነትህን የሚደፍር የሃገርህን ድንበር የሚያፈርስ መጥቷልና በእድሜህ ወጣትነት ያለህና ዓቅምህ የሚፈቅድልህ ተከተለኝ ዓቅም የሌለህና ደካማ የሆንክ ደግሞ በጸሎትህ አትርሳኝ'' የሚል በመሆኑ ጀግናው ሠራዊት ጦሩንና ጉራዴውን ይዞ ከንጉሡ ጋር ሲሠለፍ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ካህናትም በአድዋው ጦርነት በመሰለፍ ከጀግኖች አባቶች ጋር የመጨረሻውን የደም ጠብታ በመክፈል ለመጨረሻው ድል መብቃታቸውን እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በሕይወት የነበሩ አባቶች በዜና ማሠራጫዎች ሳይቀር በይፋ ሲመሰክሩ ኖረዋል ። ታሪክም ሐቁን አይስትምና ይህንኑ ያረጋግጣል ።

ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ ።



# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰብ

ከዲያ ከፍያለው መራሂ

## የክርስቲያን ጋብቻ በክርስትና ሕግ!

የጣፈጠ ማኅበራዊ ኑሮ ለማግኘት አንድ ኅብረተሰብእ የሥነ-ምግባር ፣ የሞራልና የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርት ከሥር ከመሠረቱ ከቤተ ሰብእ ጀምሮ ማግኘት ይኖርበታል ። ለቤተ ሰብእ ደግሞ መሠረቱ ጋብቻ መሆኑ የታወቀ ነው ። ከቀድሞ ጀምሮ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶችን በእውቀት ፣ በሥነ-ምግባርና በሃይማኖት ታርመውና ተኮትኩተው እንዲያድጉ ከማስተማርዋም ባሻገር ለሕጋዊ ጋብቻም የሚያበቃ የእድሜ ክልል ከ-እስከ እንደ ወሰነች ሕገ ቤተ ክርስቲያን ያስረዳል ።

በእርግጥ ከሀገር ወደ ሀገር የሰዎች ባሕል የተለያየ ስለሆነ ይሄኛው የእድሜ ዘመን ለጋብቻ መልካም ነው ብሎ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው ። ይሁን እንጅ አንድ ሰው ለኅብረተሰቡ የሚጠቅመውን ነገር በማሰብ በአእምሮም ሆነ በሰውነቱ ሲዳብር ያን ጊዜ ለጋብቻ ብቁ ስለሚሆን በዚህን ጊዜ ለጋብቻ ዝግጁ መሆኑ መልካም ነው ። ከጋብቻ በፊት የነበሩ ዓመታት በአካልም ሆነ በወኔ እንዲሁም በመንፈሳዊ ሕይወት የሚዳብሩብት ጊዜ ነው ።

እንግዲህ ወንድ ሲያገባ የስንት ዓመት እድሜ ሰው ቢሆን መልካም ነው? ልጅ አገረድዋስ የስንት ዓመት ትሁን? በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል ሴት ልጅ ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ወንድ ልጅ በሠላሳ ዓመታቸው ሥርዓተ ጋብቻቸውን መፈጸም ይችላሉ ስትል ወስናለች ። ይህም ማለት በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች እንደ እናቶች ልማድ ሙቀት ልምላሜ ሊያገኙ ይችላሉ ብሎ በማ ነብ ሲሆን ፣ በሠላሳ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወንዶችም በአካልም ሆነ በአእምሮ ብቁ ሆነው ስለሚገኙ ሕግ ሠርተው ትዳር መሥርተው መኖር ይችላሉ በማለት ቤተ ክርስቲያን ለኅብረተሰብ ሕግ ሠርታለች ።

በእርግጥ ሳይንሳዊ ምርምር ዕድገት እያሳየ ሲሄድ የኅብረተሰብም አመለካከትና የኑሮ ዘይቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ እያሳየ ይመጣል ። ለምሳሌ ቀድሞ በነበረው ሥርዓተ ማኅበር በአንድ አንድ የሀገራችን የኢትዮጵያ አውራጃዎች ወጣቶች የጋብቻ ትርጉሙ ምን እንደሆነ ሳይረዱትና እንደዚሁም ጋብቻ የሚያስከትላቸውን ሐላፊነቶች ሳያውቁ ሁለቱም ወጣቶች ለአካለ መጠን ሳይደርሱ በወላጆች ፍላጐት ብቻ የዘመድ ማውጫ መሣሪያ እየሆኑ ሲዳሩ ቆይተዋል ። ይህም ወጣቶች ወደውና አውቀው ያላደረጉት ስለሆነ ከጊዜ ወደ ጊዜ በኋላ አለመጣጣምንና መፋታትን ያስከትላል ። ያለ በቂ ምክንያት መፋታትም ለክርስትና ሕግና ለማኅበራዊ ኑሮ እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ለሁሉም ነገር ትምህርት ለኅብረተሰብእ ዕድገት ከፍተኛውንሚና የሚጫወትየ ሥልጣኔ ቁልፍ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የትምህርት በረከት ለሁሉም የሀገራችን ዜጐች ዳር እስከ ዳር እየተዳረሰ ሲመጣ ፡ የኅብረተሰብም ንቃተ ኅሊና በየጊዜው እየጨመረ ሲሄድ ፣ አጓጉል ልማዶችና ኋላ ቀር ባህሎችም ቀስ በቀስ ፣ እያዘቀጡ ሲቀሩ ፣ በአንጻሩም ታዳጊ ባሕሎች እያበቡ፣ እየሸቱና እየጐመሩ ይመጣሉ ።

ስለዚህ የኅብረተሰብን ደኅንነት ለመጠበቅ ወጣቶች ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ፣ ሥራ ይዘው ፣ በሕግ ተወስነው፣በጋብቻ ሰንሰለት ተሳስረው የኅብረተሰቡን ሕይወት እንዲኖሩ ቤተ ክርስቲያን ዘወትረ ምክርዋን ትለግሥላቸዋለች ። ቦንሆፈር የተባለው የጀርመን ሊቅ ሲናገር"እውነተኛይቱ ሕይወት ሰዎች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ቤተሰብ መሥርተው አንዱ በአንዱ በመተሳሰብ በሀሳብ ማዕበል ውስጥ ገብተው ዋኝተው ሲወጡና መኖር ሲችሉ ብቻ ነው" ይላል ። ይህም ማለት አንድ ሰው ለራሱ ብቻ የማይኖር መሆኑን አውቆ ለቤተ ሰቡ ፣ ለጐረቤቱ ብሎም ለሀገሩ ማሰብና መኖር እንዳለበት ነው ።

ጋብቻ ሰው ሠራሽ ሥርዓት ሳይሆን በእግዚአብሔር የተፈቀደ ሕግ ለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ ። ቀደም ሲል በስነ-ፍጥረት የፍጡራን ፈጣሪ እግዚአብሔር "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" ባለ ቅጽበት ለመጀመሪያው ሰው አዳም እረዳት ትሆነው ዘንድ ሔዋንን አስገኘለት ፣ ይህም ብቻ አይደለም በማኅበራዊ ኑሮ ሕግ በሥርዓት እንዲኖሩ " ብዙ ተባዙ " የሚለውን አምላካዊ ሕግ ደነገገላቸው ዘፍ ፩፣፳፰ እንግዲህ በዘመነ ብሉይ የጋብቻን ሥርዓት የወሰነው አምላክ ፣ በዘመነ ሐዲስም በቃና ዘገሊላ በሠርግ ቤት ተገኝቶ የተአምራት መጀመሪያ ያደረገው ሥርዓተ ጋብቻን እንደሆነ ታላቁ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ። ዮሐ ፪ ፩ እንግዲህ በኦሪቱም ሆነ በሐዲሱ ስለ ጋብቻ ቅድስና ተረድተናል ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ። በፍቅሩም ለሰው ጥቅምና በረከት አስቦ ይህን መልካም የሆነውን የጋብቻ ሥርዓት አቆመ ። ወንድ ሚስቱን እየወደደ እንዲጠብቃትና እንዲረዳት፣ሴትም ባልዋን እየወደደች እንድትረዳው ፣ "ጥርስና ከንፈር ቢተባበር ያምር"እንዲሉ እንደአንድልብ መካሪ እንደ አንድ አፍ ተናጋሪ ሆነው በአንድነት ልጆቻቸውን እንዲያሳድጉና በፍቅር እንዲኖሩ የፈጣሪያችን ፈቃድ ነው ።

አንድ አንድ ሰዎች ሥርዓተ ጋብቻን በሚመለከት ሁኔታ ላይ አስተያየታቸውን ሲሰነዝሩ ፣መጽሐፍ ቅዱስ ያዳላ



www.ethiopianorthodox.org

ል ብለው ይገምታሉ ። ይኸውም ሚስት ሆይ ለባልሽ "ተገዥለት" ይልና ፣ ባል ሆይ ሚስትህን "ውደዳት" ይላል እነዚህ ሁለት ቃላት ለምን ተለያዩ ፣ ለምንስ ተገዛላት አላለም ይላሉ ። እነዶ እውነቱ ከሆነ ግን "ተገዥለት" ከሚለው ቃል ይልቅ "ውደዳት" የሚለው ቃል ክብደት አለው ፣ ምክንያቱም ሐዋርያው የጻፈውን በትክክል እንዳለ ብናየው "ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት እናንተም ሚስቶቻችሁን እንዲሁ ውደዱ" ኤፌ ፭፥፳፭ ይላል ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ሲወዳት ራሱን እስከ መሠዋት ፣ ሥጋውን እስከመቁረስና ደሙንም እስከማፍሰስ ደርሶላታል ፣ የእውነተኛ መውደድም ትርጉሙ ይህ ነው ። "ፍቅርም እንደዚህ ነው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን፣ ስለኃጢአታችንም ማስተስረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም" ፩ኛ ዮሐ ፬፥፲ ስለዚህ ነው "ውደዳት" የሚለው ትዕዛዝ "ተገዥለት" ከሚለው ይልቅ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ።

ሚስቶችንም ለባሎቻችሁ ተገዙላቸው ሲል ሊገዙ የሚችሉት በፍቅር ነውና ለእነርሱም የተሰጠውን ትዕዛዝ አቅልለን አናየውም ። ሚስቶችም ቢሆኑ ለባሎቻቸው እያሰቡና በሚያስፈልጋቸውም መንገድ በሚችሉት መጠን እየተንከባከቡ ማኖሩ ግዴታቸው ይሆናል "ባል ለሚስቱ የሚገባውን ያድርግላት እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ ፤ ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም ፣ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም ፤ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ ፤" ፩ ቆሮ ፯፥፫-፬ እንዲህ እያለ ሐዋርያው የባልና የሚስትን ሕይወት እያስተካከለ ያቀርበዋል ።

እንዲሁ ሴት ባልዋን ለመርዳት ስታስብ ወንዱ ደግሞ ሚስቱን ለመጥቀም ማሰብ ይገባዋል ። ባልና ሚስት በፍቅር አንድነት ተሳስረው እርስ በርሳቸው መተሳሰብ ይገባቸዋል ።

ስለዚህ ወንዶች ሚስቶቻቸውን ቢንቁ የፈጣሪያቸውን ሀሳብና ፈቃድ መተላለፋቸው ነውና በጋብቻ ያለውን በረከትና ደስታ ያጣሉ ። ማኅበራዊ ኑሮአቸውም የተሰነካከለ ይሆናል ። አንድ ደራሲ ሲናገሩ የሕዝቡ ኑሮ መሠረት የቤተ ሰብእ ኑሮ ነው ። የቤተ ሰብእም ኑሮ መሠረት ጋብቻ ነው ። ጋብቻም በእግዚአብሔር በጐ ፈቃድ የተመሠረተ ነው ።

ስለዚህ ጋብቻ እግዚአብሔር እራሱ ለሰው ጥቅም እንዲሆን ያቆመው ሥርዓት እንደሆነ አስተውለን ብናከብረው ለራሳችን በረከትና ደስታ ብቻ ሳይሆን ለሕዝባችን ክብርና ጥቅም ይሆናል ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ንቆ የጋብቻን ሥርዓት በመልካም የማይጠብቀው ሰው ግን እራሱን ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ያስነውራል ። የጋብቻን ሥርዓት የማያከብር ሕዝብ ብርቱ ጤናማም ሕዝብ ለመሆን ከቶ አይችልም ይላሉ ።

ስለዚህ ለኅብረተ ሰብኡ ደኅንነትና ሰላማዊ ኑሮ በማሰብ የክርስቲያን ጋብቻ በክርስትና ሕግ እንዲሆን ቤተ ክርስቲያን ዘወትር ምክርዋን ትለግሳለች ።

# የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ

በሐዋርያት አንድነት ውስጥ ያዕቆብ በሚል ስም የሚጠሩ ሶስት ሐዋርያት አሉ ። እነርሱም የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ የጌታ ወንድም የሚባለው ያዕቆብና የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ናቸው ።

ከእነዚህም ከሦስቱ ሁለቱ በሐዲስ ኪዳንና በገድለ ሐዋርያት ሰፋ ያለ ታሪክ አላቸው ። ለእልፍዮስ ልጅ ለያዕቆብ ግን ብዙ ታሪክ አልተጻፈለትም ። በሐዲስ ኪዳንም በሐዋርያት የስም ዝርዝር ላይ ስሙ ብቻ ከመጠቀሱ በቀር ሌላ ዝርዝር ታሪክ የለውም ። /ማቴ. ፲፥፫ማር ፫፥፲፰ ። ሉቃ ፮፥ ፲፭ የሐዋ ፩፥፲፫/ ። በትውፊትም ስለ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ብዙ ታሪክ የለም ።

አንዳንድ ሊቃውንት ይህ ያዕቆብ የቀራጩ ማቴዎስ ወንድም እንደ ነበር ተርከዋል።ለዚህም የሚያቀርቡት ማስረጃ የሁለቱም አባት እልፍዮስ መባሉን ነው ። ማር ፪፥፲፬ የያዕቆብንና የማቴዎስን ወንድማማችነት የተቀበሉት እነዚሁ ሊቃውንት ታሪካቸውን በመቀጠል ያዕቆብ ቀናተኞች ከሚባሉት ወይም የሮማውያንን የቅኝ መንግሥት ይቃወሙ ከነበሩት ወገኖች ክፍል ሲሆን ማቴዎስ ደግሞ ከሮማውያን መንግሥት ጋር ተስማምቶ በወንጌሉ እንደ ተገለጠው ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ በመያዝ ይኖር እንደነበር ጽፈዋል ።

አዎ ይህ አስተያየት ልክ ሊሆን ይችላል ። ምክንያቱም በሐዋርያት አንድነት ውስጥ ሌሎች ብዙዎች ወንድማማቾች ይገኛሉና ። ለምሳሌ፡-የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ የዮና ልጆች ጴጥሮስና እንድርያስ የዮሴፍ ልጆች ያዕቆብና ይሁዳ ለሐዋርያነት በአንድነት ተጠርተዋል ። በዚህ አንፃር ሁለቱ የእልፍዮስ ልጆች ማቴዎስና ያዕቆብ ምሊጠሩ ይችላሉ ።

ቅዱሳን ታሪክ መድበል የሆነው መጽሐፈ ስንክሳር ስለ እልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡-ያዕቆብ በየሀገሩ ወንጌልን ካስተማረና ብዙኃን ሕዝብን ካሳመነ በኋላ በመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ በቤተ መቅደስ አስተማረ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ስለ ሰዎች ቤዛ በመስቀል ላይ መሞቱን መነሣቱንና ማረጉን መሰከረ ።በዚህ ጊዜ አይሁድ ወደ ንጉሥ ቀላውዴዎን ወስደው ከቄሣር የተለየ ሌላ ንጉሥ እንዳለ ይናገራል በማለት ከሰሱት ንጉሡም በድንጋይ ደብድበው እንዲገድሉት አዘዘ ። በትእዛዙም መሠረት እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር የካቲት 10 ቀን 60 ዓ.ም. በድንጋይ ወግረው ገደሉት። በገድለ ሐዋርያትም ስለ ያዕቆብ የተጻፈው ታሪክ በስንክሳር ከተጻፈው ልዩነት የለውም ።

በዘመኑ የነበረው በታሪክ ጸሐፊነቱ የታወቀው ዮሴፉስ ያዕቆብ ጳጳስ እንደነበረ ከገለጠ በኋላ በድንጋይ ተደብድቦ መሞቱንም ጨምሮ ተናግሮአል ።

ከዮሴፉስ በኋላ አንድ መቶ ዓመት ቆይቶ የክርስትና እምነትን የተቀበለው አይሁዳዊው ሄጊስጳስ ደግሞ ስለ እልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ እንደሚከተለው ጽፎአል፡-ያዕቆብ በኢየሩሳሌም በሚያስተምርበት ጊዜ አይሁድ በቤተ መቅደስ ተድባብ/ጫፍ/ አውጥተው አቆሙት ። በዚያም ላይ ሆኖ ክርስቶስን እንዲክድ ጠየቁት ። ባይክድ ግን ከቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ወርውረው እንደሚጥሉት አስፈራሩት ። እርሱ ግን ክርስቶስን በመካድ ፈንታ በክርስቶስ ላይ ያለውን ፍጹም እምነት በቆመበት ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ መሰከረ ። "ሥጋዬን ወውሩት ፡ ነፍሴን ግን ክርስቶስ እጆቹን ዘርግቶ ይቀበላታል" ሲል ተናገረ ። ይህንም ተናግሮ እንደፈጸመ በቤተ መቅደሱ አደባባይ የተሰበሰቡት አይሁድ ከቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ገፍተው ጣሉትእንደ ወደቀም በድንጋይ ወግረው ገደሉት።

እንደ ምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ደግሞ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ በፔርሽያ/በፋርስ/ ወንጌልን ካስተማረ በኋላ በዚያው በመስቀል ተሰቅሎ እንደ ሞተ ይተርካል ።

ይሁን እንጂ ይህ ታሪክ በብዙዎች ዘንድ ተደጋፊነት ያለው አይመስልም ። ስለዚህ ታላቁ ታሪክ ጸሐፊ ዮሴፋስና ሄጊስጳስ የተባበሩበት በስንክሳርና በገድለ ሐዋርያት የተጻፈው የያዕቆብ ታሪክ በብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት አለው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ይህን ትቀበላለች። በየዓመቱም የካቲት ፲ ቀን በዓሉን በጸሎት ታከብረዋለች ምእመናችዋም በአማላጅነቱ እንዲማፀኑ ታስተምራለች ።

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ቀድሞ ለእስራኤል መንግሥት ቀናተኛ እንደነበር በኋላ ለእግዚአብሔር መንግሥትና አምልኮት ቀናተኛ በመሆን እስከ ሞት ደርሶአል ። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ፈለግ በመከተል ለእግዚአብሔር መንግሥትና አምልኮት መንፈሳዊ ቅንዓት ያላቸው መምህራን ሊኖሯት ያስፈልጋል ። በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንፃለችና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

# ኃላፊነትን መዘንጋት

ኃላፊነትም ማለት ማንኛውም ሰው የያዘውን ሥራ የሚሰራና በታማኝነት ሕዝብን ለማገልገል የተሰለፈ መሆኑን የሚያውቅ ማለት ነው ። እንዲህ ያለውም ኃላፊነት ታማኝነትን እንጂ ጾታን አይጠቅም።ይህም በመሆኑ ይብዛም ይነስም ከፍተኛም ይሁን ዝቅተኛ ኃላፊነት ያልተሰጠው ሰው በአለም ላይ አይገኝም ።

ለምሳሌ ወላጆች ለወለዱአቸው ልጆች ታላቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው የታወቀ ነው ። ስለዚህ በምግብ እየተንከባከቡ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን በመፍራት በሀገር ፍቅር፣ በትምህርት በመልካምጠባይ ኮትኩቶ ማሳደግ ይኖርባቸዋል ። አሳድገውም ለቁም ነገር የማድረስና በእግራቸውም እንዲተኩ የማድረግ ኃላፊነት የነሱ ስጦታ ነው ።ይህን ባያደርጉ ግን ኃላፊነታቸውን ዘነጉ ማለት ነው ።

መምህራንም ተማሮችን የማስልጠንና የማስተማር ኃላፊነት አለባቸው። ይህውም በትምህርት አንጸው በእውቀት ገንብተው የሻከረ ጠባያቸውን በሞራል አለስልሰው በጠቅላላው አዕምሮአቸውን ብሩህ!አድርገው ለሀገራቸው ብዙ ምሁራንን የማበርከት ኃላፊነት የተጣለው በነሱ ላይ ስለሆነ ነው ። ይህን ባያደርጉ ግን ኃላፊነታቸውን ዘነጉ ማለት ነው ።

እረኞችም ስለበጎቻቸው ታላቅ ኃላፊነት ተሰጥቶአቸዋል ይህውም አውሬ በመጣ ግዜ ጥለዋቸው እንዳይሸሹና ሕይወታቸውንም ስለበጎቻቸው እንዲለውጡ የለመለመ ሣር ፣ጥሩውኃ ወዳለበት እንዲያሰማሩ ይፈለግባቸዋል ። ለምሳሌ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ የነበሩት የበጎችን እረኛ ታሪክ የተመለከትን እንደሆነ እረኛ የሚሄደው ከበጎች ፊት ነበር ። ከዚያ በኋላ በጎች ይከተሉታል ። ገደልም ቢኖር ገደል ውስጥ ገብቶ እረኛው ለበጎቹ መንገዱን ለቆ እያሳየ መሄድ ነበረበት ወንዝም ቢኖር ወንዙን ተሻግሮ እረኛው ለበጎቹ መስመሩን ማሳየት ነበረበት በዚህም ጊዜ ነበር በጎቹ እየተከተሉት የሚሄዱት የመልካም እረኛ ምሳሌ ይህ ነው መልካም እረኛ ነፍሱን ስለሌሎች ይሰጣል አስቀድሞም ይጋፈጣል የመከራውንም ሆነ የችግሩን ጽዋ የመጀመሪያውን የሚቀምሰው ዋናው እረኛው ነው ። ይህንን የማይፈጽም እረኛ ቢኖር ግን ኃላፊነቱን እንደዘነጋ ያስቆጥረዋል ።

እንዲህ ያለውም አባባል ሕይወቱን ስለ በጎቹ የሚለውጥ ቸር እረኛ እንዳለና ኃላፊነትም የሚሰማው መልካም ጠባቂ እንዳለ ያመለክተናል በሌላ በኩል ደግሞ ተኩላ በመጣ ግዜ በጎቹን ትቶ የሚሸሽና ኃላፊነቱን ዘንግቶ ምንደኛ የሆነ እረኛም መኖሩን ያሳስበናል ። ለምሳሌ አንድ የመንጋ ባለቤት የሆነ ጠቦቶቹን በጎቹን ጠብቅ ለሠራተኛው ዋጋው ይገባዋል በሚለው መጠን ዋጋህን እከፍልሃለሁ ሲል አንድ እረኛ ቀጠረ ። እረኛውም በውሉ መሠረት አደራውን ተቀብሎ በጎቹን ይጠብቅ ጀመር ። እረኛውም ምንደኛ እንጂ እውነተኛ እረኛ ስላልነበረእሱን ከመሰሉትም



www.ethiopianorthodox.org

ንደኛ ከሆኑት እረኞች ጋር ሆኖ የዱር ፍሬ እየለቀመ ለራሱ ይበላ ጀመር ከዛፍ ጥላ ስርም አርፎ ከንደኞቹ ጋር ከመጫወት በቀር በጎቹ የት እንዳሉ ምን እንደ ሚመገቡ አይመለከትም ነበር አውሬም ቢበላቸው የትም ባዝነው ቢጠፉ ግድ የለሽ ነበር ።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ በጎቹ ጠፉበት ከአፋፍ ብቅ ብሎ የመንጋውን ባለ ቤት ጠራ ። ባለቤቱም ምን ሆነሐል ብሎ ጠየቀው በጉቹጠፍተዋልና እንዲያፋልጉኝ ነው ሲል መለሰለት ባለቤትየውም ጠቦቶቹና ግልገሎቹስ አሉ ወይ? ብሎ ቢጠይቀው እነሱማ ገና ጠዋት ነው የጠፉት አሁን ግን የቸገረኝ ታላላቆቹ በጎች ስለጠፉብኝ ነው ሲል መለሰለት ይባላል፣

እንደዚህ እረኛ ኃላፊነታቸውን የዘነጉ አንዳንድ የመንፈሳውያን መሪዎች በዘመናት መካከል አልፎ አልፎ/ተነስተው እንደነበረ ከመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ። እነዚህንም ለመረጃ እንዲሆን በማለት ጥቂቶቹን በቅደም ተከተል አቅርበናቸዋል ።

ካህኑ አሮን ለሙሴ አፍና አስተርጓሚ እንዲሆን የተሰጠ ታማኝ ሰው ነበረ።ሙሴ አሥሩን ሕግጋት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመቀበል በሲና ተራራ ለአርባ ቀን ያህል ቆየ ። በመዘግየቱም ትኩል የሆነው የአይሁድ ህዝብ በቃል ፣በመንፈስ ፣ በድምጽ ጠዋት ማታ የሚያነጋግረውን እግዚአብሔርን ክዶ ሰው ሰራሽን ጣዖት እንዲያቆምለት አሮንን ጠየቀ አሮንም የእግዚአብሔር ወኪልና እንደራሴ መሆኑን እረስቶና ኃላፊነቱንም ዘንግቶ ሕዝቡ ያዋጣውን ወርቅ በመቀበል በመቅረጫው ቀረጸው ። ቀልጦ የተሰራ ምጥጃ አደረገው እርሱም እስራኤል ሆይ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክት እኒህ ናቸው አለ ። መስዋዕትም የሚሰዋበትን ስራለት ነገም በዐል ነው ሲል አወጀ ሕዝቡም በአዋጁ መሠረት የሚቃጠል መስዋዕት ለጣዖት የደህንነትም መሥዋዕት አቀረቡ ሕዝቡም ሊበሉና ሊጠጡ ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ“ ኦሪት. ዘጸአት ምዕራፍ ፴፪፣ ፬-፮ ።

ከዚህ ላይ አንድ አይነት ትምህርት ልንወስድ እንችላለን ካህኑ አሮን ቀደም ብሎ የእግዚአብሔርን አምላክነት ጌትነቱንና ክብሩን ለሕዝቡ አስተምሮ ቢሆን ኖሮ በሕዝቡም ላይ ሆነ በራሱ ላይ ይህ ችግር ባልደረሰም ነበር ። ባለማስተማሩ ግን ሕዝቡም እራሱም ጣዖት እንዲያመልኩ ሆነ ይሁን እንጂ ካህኑ መንፈሳዊ መሪ እንደመሆኑ መጠን ከሕዝቡ ጋር መተባበሩን ትቶ ማስተማርና መገሰጽ በተገባው ነበር ። ይህም ባይሳካለት መታሰር ወይም መሞት ይገባው ነበር እንጂ ከሚመራው ህዝብ ጋር ሆኖ ለጣዖት መንበርከክ አልነበረበትም ። ሆኖም ፈሪና መስሎ አዳሪ በመሆኑ ኃላፊነቱን እንደዘነጋው ከተግባሩ ልንረዳው እንችላለን ።

በመጨረሻ ግን ሙሴ ከሄደበት መጥቶ የሚያመልኩትንም ጣዖት ሰብሮ ጥሎታል ያመለከውንም ህዝብ ቀጥቶታል ። አሮንን ገስጾ ወደ ንስሐ እንዲመለስ አድርጎታል ። አሁንም ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው እንደ አሮን ያለ ኃላፊነቱን ዘንግቶ መስሎ የሚያድር ካህን ሳይሆን እንደ ሙሴ ያለ በንስሐ የሚቀጣና የሚገስጽ ካህን ነው ።

ዮናስም የነነዌን ሰዎች እንዲያስተምር ከእግዚአብሔር ጥሪ ደርሶት ነበር። እሱ ግን ጥሪውን አልተቀበለም ጀርባውን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ወደፊቱ ከበለለ ያመለጠ ቢመስለውም ከእግዚአብሔር እጅ አላመለጠም በእግዚአብሔር እጅ ከተቀጣ በኋላ መጀመሪያ ወደ ተጠራበት ቦታ ሂዶ አስተምሮ አሳምኖአል ።

ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር ማንን እልካለሁ እያለ ጢትማታ የወንጌልን መልክተኞችን ይጠራል ። አንዳንድ መምህራን ግን እንደ ዴማስ ዓለምን ከመውደዳቸው የተነሳ በደስታና በምቾት ለመኖር ጥሪውን አልተቀበሉም እንደ ዮናስ ወደፊታቸው በመኮብለል ላይ ይገኛሉ ። አንዳንዶቹም ጥሪው ሲደርሳቸው ንብረታችን ትተን ፡ ከቤተሰባችን ተለይተን፣ምቾትና መብራት ካለበት ከከተማ ኑሮ ወጥተን መብራት ከሌለበት ገጠር ሄደን መኖር ደስ አይለንም እያሉ የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብለው ወንጌልን እየተዘዋወሩ ለሕዝብ ማስተማር ደስ አይላቸውም ይህም የሚያሳየው እነሱ ካወቁ ፣ እነሱ ከተማሩ፣ሌላው ባያውቅ ፣ባይማር ሌላው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ባይሆን ግድ የለሾች መሆናቸውን ነው ። ጥቂቶቹ ደግሞ ሥራቸውና ስማቸው መንፈሳዊ ሆኖ ሳለ መጽሐፍ ቅዱስ በእጃቸው ይዘው መታየትና በሕዝብ ፊት ስለ ክርስቶስ መመስከር ደስ አይላቸውም ሐፍረት መስሎ ይታያቸዋል ።

ይህ ሁሉ ኃላፊነትን መዘንጋት ነው።

ስለዚህ እያንዳንዳችን ካህን እንደመሆናችን መጠን በኃላፊነት በእረኝነትና ሌላውን እንድናገለግል ተጠርተናል መጋቢነትንም ተሹመናል ። ለዚህም መረጃ የሚሆነን ወንጌላዊው ሲጽፍ ሥጋዊ ኃላፊነት ያለው የአሕዛብ አለቆች ለመከበርያ ሌላውንም አዝዞ ለመኖር ነው የሚሾሙት ። የኛ የመንፈሳውያን እረኞች ኃላፊነት ግን ከዚህ በጣም ለየት ያለ ነው ። ኃላፊነት ማለት ታዛዥነት ከመባሉም ሌላ ሕዝብን የሚያገለግልና የክርስቶስን አገልግሎት የሚያደርስ ተላላኪ ማለት ነው ለክርስቲያን የተሰጠ ኃላፊነት ይህ ነው ።

እንዲህ ያለው ኃላፊነት በተሰጠን ጊዜ ሕዝቡን የምንመግበው ምን ዓይነት ምግብ ነው? የሚል ጥያቄ ይቀርብ ይሆናል ። በመንፈስ የተራቡትን ምዕመናን እስኪጠግቡ ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል ልንመግባቸው ይፈለግብናል መልካም መጋቢዎች ሁነን ብንገኝ ዋጋችን ክብር ሲሆን ክፉ መጋቢዎች ብንሆን ደግሞ የመጨረሻ ዋጋችን ውርደት ከዘለፋ ጋር ነው ከሥራ ፈትነትም ይህን የመሰለ መጥፎ ጠባይ ስለሚወረስ የክርስቶስ መጋቢዎች ሁነን ከተሾምን ጠባያችን እንዲያምር የሥራ ሰዎች መሆን ይገባናል።በታማኝነትየተቀበልነውን ምኃላፊነትእንዳንዘነጋ ሁልጊዜእራሳች

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# የግብርና በረከት

ገበሬ ለተጠቃሚው ክፍል ከግብርና የሚገኘውን በረከት ሊያስገኝ የሚችለው የሚያርስበት በሬና ራሱ የተሟላ ጤንነት ለማግኘት ሲችል ነው ፣ ከዚህም ጋር የተሟላ ጠንካራ አገልግሎት ለመስጠት በምግብ በኩል ተመጣጣኝ መኖ ማግኘት ያስፈልገዋል ።

በግብርና ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚወጣው “ “ዜና ግብርና” የተሰኘው መጽሔት ለአንባብያን የሚያቀርበው ፍሬ ሃሳብ የግብርና በረከት ተትረፍርፎ ሁሉም በየረድፉ ተገቢውን ፍላጐት እንዲያገኝ የሚያደርግ ነው ።

ገበሬው በእርሻ አስተራረስ ፣ በአዝርእት አጠባበቅ ፣ በእርሻ አገልግሎት የሚጠቀምባቸው እንስሳት በጤናቸው ረገድ የሚጠበቁበትን ፣ ለሰውና ለእንስሳት ጐጅ የሆኑ ተባዮችን ለማጥፋትና እነዚህም ምንና ምን እንደሆኑ ባለሙያዎችን እያቀረበ በቂ ትምህርት ይሰጣል ።

ገበሬው ከባለሙያዎች የሚቀርብለትን ገለጻ በተግባር እየገለጸ ከሚደርስበት ችግር ይላቀቃል።ቅድስንቤተ ክርስቲያንም ይህን ዓለማ በመከተል ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር በማገናዘብ ይህ መልእክት ላልደረሳቸው ክፍሎች ይዳረስ ዘንድ ከግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ክፍል ጋር በመስማማት ከመጽሔቱ ላይ የሰፈሩትን ፍሬ አሳቦች ታስተላልፋለች ።

በዛሬው ጽሑፍ ዜና ግብርና ቅጽ + ቁጥር 2 ጥቅምት 75 ዓ.ም. ገጽ 6 “ባለሙያው ይናገር” በሚለው ዓምድ ላይ 3 ባለሙያዎች የሰጡትን ትምህርት እናቀርባለን ባለሙያዎች ዶክተር ዘለቀ ዳኛቸው ዶክተር ኃይለማርያም ለሚቻ ፣ አቶ ሰሎሞን አድማሱ ሲሆኑ እነሱም ለገበሬው ጠቃሚነው ብለው የሰጡት ገለጻ ስለቆላ ዝንብና የገንዴ በሽታ መነሻነትና ጐጂነት ነው ። “የቆላ ዝንብ በዘልማድ ሲታይ ከተራው ዝንብ የአካልም ሆነ የባሕርይ ልዩነት አለው” ካሉ በኋላ ዝንቡ እንዴት ሊራባ ስለሚችልበት መንገድ ሲገልጹ ዝንቡ የሚራባው በቀጥታ ግንኙነት ሲሆን በማኅፀን ከእንቁላል ወደትል ነት ተለውጦ እስኪወለድ ድረስ ከ10-12 ቀናት ይወሰድበታል”.....ካሉ በኋላ ስለዝንቦች ዕድሜ ሲያወሱ “የዝንቦች ዕድሜ ለሴቷ ከ30-60 ለወንዱ 30 ቀናት አካባቢ ይሆናል



የጤና ባለሙያዎች ለእንስሳት ሕክምና ሲሰጡ

እስከአሁን ድረስ በተደረገው ጥናት የአየሩ ሁኔታ ቀዝቃዛ በሚሆንበት ጊዜ ሴቷ 190 ወንዱ 150 ቀናት መቆየት ይችላሉ፣ ዝንቡ የሚኖረው ዛፍ ፣ ቁጥቋጦ ፣ ጫካና ሣር በበዛበት ውሃ አመች በሆነበትና ከ18-32 ሴንቲ ግሬድ የሚሆን የአየር አካባቢ ሙቀት ባለው ቦታ ነው ለሕይወት አስጊ የሚሆነው የአየር (አካባቢ) ሙቀት መጠን ዝቅተኛው 7 ሲሆን ከፍተኛው 40 ሴንትግሬድ ነው ። ይህ ዝንብ አንድ ጊዜ እስኪጠግብ ድረስ ከተመገበ እስከ ፫ ቀን ድረስ ያለ ችግር ይኖራል” ይላሉ የቆላ ዝንብ ቀደም ሲል በየት እንደታወቀ ሲያመለክት በሰሜን አሜሪካ ፣ በእስያ ፣ በደቡብ የመን እንደነበረ ሲታወቅም በአሁኑ ጊዜ በአፍሪቃ ክፍለዓለም ብቻ ተሠራጭቶ እንደሚኖር ታውቆአል ይኸም በስፋት አስር ሚሊዮን ካሬ ሜትር የሸፈነ ሲሆን ዝንቡ 31 የተለያዩ ዓይነት እንዳለው ተገልጾአል ።

በአገራችንም 98.000 (ዘጠና ስምንት ሺህ) ካሬ ኪሎ ሜትር የሸፈነ ሲሆን አገሪቱ ካላት የመሬት ስፋት 8% ይሆናል ማለት ነው ይህ ዝንብ ለመጀመሪያ ጊዜ መኖሩ የታወቀው በ1845 ዓ.ም. ሲሆን የተገኘውም በባሌ ክፍለ ሀገር በወልመል ወንዝ አካባቢ ነው ይህ ምርምር በውጭና በሀገር ሊቃውንቶች ሲካሄድ ቆይቶ ዛሬ ወደ 5 ዓይነት ይገኛል አሁን ግን ጥናቱ ከ1970



www.ethiopianorthodox.org


ዓ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ብቻ ሆኖአል ።

ይህ ዝንብ የሚያደርሰውም ጉዳት ተጠቃሎ ሲታይ የገንዲ በሽታን ማስተላለፍ የእንስሳትን ደም መምጠጥ በዚህ ሳቢያ በሚፈጠረው ቁስል ሌላ በሽታ መፈጠሩ ነው ።

ቀደም ሲል በተደረገው ጥናት በልዩ ልዩ ክፍላተ ሀገራት ለምሳሌ በጐጃም፣ በጋሞ ጎፋ ፣በከፋ፣ በኢሉባቦር በሲዳሞ ፣ በሸዋና በወለጋ ቆላማ አካባቢዎች እንስሳትን የሚያጠቃ መሆኑ ተደርሶበታል ።

የገንዲ በሽታ ፣ይህ በሽታ በመብዛትና በማነስ መጠኑ ይለያይ እንጂ በማንኛውም ክፍለ ዓለም ይገኛል ፣ በሽታውሉ ። በሽታውን የማከሙና የመከላከሉ ጥረትም የሀገሪቱ አቅም በሚፈቅደው መጠን በየዓመቱ ሕክምናው ቢደረግም ከሃያ ሺህ ያላነሱ ከብቶች ይሞታሉ።

የበሽታው ዋና ዋና ምልክቶች ክሳት ትኩሳት ፣ ደም ማነስና እብጠት ናቸው በሽታው ሲጀምር በሮችን የሥጋና የጉልበት ኃይልን በማሳጣት ፣ የፀነሱ ላሞችን በማስጨንገፍ ፣ ጥጆችንና ላሞችን በመግደል የእንስሳት ተዋፅኦ እጥረትን ይቀንሳል ። በድምሩ የኤኮኖሚ ቀውስ ያመጣል ማለት ነው ከበሽታው ፍራቻ የተነሳ ሰዎች በቆላማ አካባቢዎች መኖር ስለማይፈልጉ ቆላማ ቦታዎች ምንም ልማት ሊካሄድባቸው አልቻለም ነበር ፣ አሁን ግን ቆላማ ቦታዎች በሰዎች ተጣበው ይገኛሉ'' ይሉና እነዚህን ጠንቆች ለማጥፋት ልዩ ልዩ ችግሮች መኖ.



በድርቅና በገንዲ በሽታ እልቂት የደረሰባቸው እንስሳት

ሰውንና እንስሳትን አጠቃሎ የሚያጠቃ በመሆኑ የሚያሰጋ ነው ይህ የገንዲ በሽታ ሌላውስሙ "ወዝውዝ" ይባላል በሀገራችን በአሁኑ ወቅት ሰባት ዓይነት ሲገኝ ስድስቱ እንስሳትን አንዱ ሰውን የሚያጠቃ መሆኑ ታውቆአል በተለይ በሰው ላይ የእንቅልፍ በሽታ ያመጣል የገንዲ በሽታ (ሃያ ስድስት ሚልዮን ) 26.000.0000 ከሚሆኑ የጋልጋ ከብቶች በየዓመቱ መካከል ከአስር ሚልዮን) 10.000.000 በላይ ይጠቃራቸውን ጠቁመዋል ለምሳሌ ያህል መድኃኒቱ ሲረጭ በደኖች ላይና በዱር አራዊቶች ላይ ፣ በየብስ በንቦች በባሕርም ውስጥ በአሳዎች ላይ ጉዳትን እንደሚያስከትል ቢታወቅም በረቂቅ አሠራር እነዚህን ጠንቆች በማጥፋት ገበሬዎች የግብርና ሥራቸውን በሰላም እንደሚሠሩ እየተደረገ ነው ።

(ገበሬዎች) አርሶ አደሮች ከራሳቸው ጤንነት ጋር የከብቶቻቸው ጤንነት ካልተጠበቀ አርሶ መና እንዳይሆኑ የሚደረገው ጥረት አኩሪ እየሆነ ሄዶአል ብለዋል ።

እንግዲህ ከባለሙያዎች እንደተገለጠውና ሌሎች የጤና ባለሙያዎች የጤና መጻሕፍት እንደሚያስረዱት ዝንብ ያውም የቆላ ዝንብ ጠላታችን መሆኑን መገንዘብ አለብን ፣ ከዝንብ ፣ የበለጠ ጠላት እንደሌለንም በሕፃናት ልጆች ላይ የሚያደርሰውን የጤና ጠንቅና ጉዳቱን ማስታወሱ ይጠቅማል ።

የገንዲ በሽታም በእንስሳት ከብቶቻችን ላይ እንዲሁም በሰዎች ላይ ከሚያደርሰው አደጋ ሌላ ፣ በበሽታው የተበረዙ ላሞች ወተት እንዳይሰጡ ፣ በሮች ሥጋቸው እንዳይበላ ከማድረጉም ሌላ በቆዳቸው ረገድም በሽታው ከጥቅም ውጭ ስለሚያደርገው ከቆዳ የምናገኘው ምንዛሪ እንዲቀንስ ምክንያት ይሆናል።

እግዚአብሔር አምላክ ከብቶች እንዲረቡ ከበሽታ እንዲድኑ ትእዛዜንና ሥር

በገጽ ፮ ላይ ይመልከቱ

## ኃላፊነትን መዘንጋት

ከገጽ ፲፪ የዞረ

ንን መቆጣጠር ይገባናል።ተጠርተንም የምንሾመው የእግዚአብሔርን ቃል የተጠሙትን ነፍሳት ለማርካት ነው ።

ስለዚህም ኤርምያስ ቃልህ ተገኝቶ አል።እኔም በልቸዋለሁ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ!በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነኝ ሲል ተናግሮአልና ኤር. ፲፭ ፥ ፲፮ ።

እኛም የእግዚአብሔርን ቃል ለምእመናን መጋቢዎች ስለሆን ኃላፊነታችንን አውቀን ቃሉን እንመግብ የመምህራን ተግባርና ኃላፊነት ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ቅዱስ ላሊበላ

ስመ ጥሩው ጻድቅ ላሊበላ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ዓፄ ድልነዓድ ዘመነ መንግሥት መናገሻ ከተማ የነበረውን የአክሱምን መናገሻ ከተማ ሰርዘው በላስታ ሮሃ ላይ አዛውረው 333 ዓመት ከነገሡት ነገሥታት 11ኛ ንጉሥ ነበር ። የነዚህም ነገሥታት ስም ዝርዝርና ነገዳቸው እንደዚህ ነው መራ ተክለሃይማኖት የተባለው ሰው የዓፄ ድልነዓድ ጦር አዛዥ ነበር የንጉሡን ልጅ መሶበ ወርቅን አግብቶ መንግሥቱን ገልብጦ መናገሻ ከተማውን በላስታ ሮሃ ላይ መስርቶ ስመ መንግሥቱን ዛጔ በሚል ስም ሰይሞ በ920 ዓ.ም በመላ ኢትዮጵያ ላይ ነገሠ ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ስም ዝርዝርና ታሪካቸውም እንደዚህ ነው ጠጠውድም ግርማ ስዩም ዛን ስዩም መይራሪ ሀርቦይ ትርድአነ ገበዝ እነዚህ ልጆቹ ሲሆኑ የልጅ ልጆቹ ደግሞ ቅ ይምርሃ ቅ ሐርቤ ቅ ላሊበላ ቅ ነአኩቶለአብ አቤቶ ይትባረክ ናቸው ከላይከፍ ብሎ በ3ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ጃን ስዩም የተባለው ሰው ዐጽፍተ ወርቅ የምትባል ሴት አግብቶ ሐርቤንና ዮዲት የተባለችውን ሴት ልጅ ከወለደ በኋላ ሚስቱ ሞተችበት በዚህ መካከል አስቀድሞ ወራሴ መንግሥት ስለተባለ የዋግ ተወላጅ የሆነች ኪርወርና የምትባል ሴት አግብቶ ከወንድሙ ቀጥሎ ነገሠ ሚስቱ ኪወርናም የቢሃትእመቢት ተብላ ንግሥት ተባለች በዚህም መካከል ሚስቱ ኪርወርና ፀንሳ በ1142 ዓ.ም ታኅሣሥ 29 ቀን ወንድ ልጅ ወለደችለት ይህ ሕፃንም የተወለደ ዕለት የንብ ሠራዊት ወደቤተ መንግሥቱ ውስጥ መጥቶ ሕፃኑ ከተወለደበት ዕልፍኝ ውስጥ ገብቶ መላ አካላቱን ወሮ ዙሪያውን ከበበው እናቱም ያን አስደናቂ ነገር ተመልክታ ልጇን ንብ በላው ልጇን ንብ ከበበው ልጁ ማር ይበላል ንብ ጌታውን አወቀ ስትል እንደመሰላት "ላል ይበላ"ብላ ስም አወጣችለት ላል ማለት በዓገውኛ ቋንቋ የንብ ማር ወይም ንብ ማለት ሲሆን ይበላ ማለት ደግሞ ማር ይበላል ማለት ነው ። ስለዚህ እናቱ እንደመሰላት ይህን ስም አወጣችለት ይህ ስመ ጥሩ ልጅ ቀስ በቀስ እያለ አደገ 8 ዓመት ሲሆነው ፊደል ቆጠራ ጀምሮ ዳዊትና ቅዳሴ ተምሮ ዲያቆን ሆነ ከመልኩ ደምግባትና ከግርማው የተነሳ ትንሹም ትልቁ ይህ ልጅ ይነግሣል እያለ ይተነብይለት ጀመር በዚህም ወሬ ንጉሡና ቢትወደዶቹ ቅንዓት አደረባቸው በዚህም መካከል የላሊበላ እናትና አባቱ ስለሞቱበት ከትልቅ ወንድሙ ጋር ተቀመጠ ትልቅ ወንድሙ የተባለውም ሀርቤ ስመ መንግሥቱን ገብረ ማርያም ብሎ የነገሠው ነው የንጉሡ ገብረ ማርያም የእናት አባቱ ልጅ ዮዲት የተባለችውም ለጊዜው የዕለት ጥቅሟን በመፈለግ የአባቷን ልጅ ወንድሟን በመርዝ ለመግደል አመች ቀን ትፈልግለት ነበረችና ከዕለታት አንድ ቀን ለላሊበላ ኮሶ ታየውና መድኃኒት ጠጣ በዚህ ጊዜ ይህች እኅቱ የኮሶ ማርከሻ ብላ መርዙን ከመጠጥ ጋር ቀላቅላ ላከችለት ያንንመጠጥ ከላሊበላ ፊት የማይለይ አሽከሩ ተቀብሎ ቀምሶ ለመስጠት ሲራመድ መርዙ አዙሮ ጣለውና አስታውኮት ሞተ ከዚያ የነበረውም ውሻ ትውኪያውን ቀምሶ ሞተ ላሊበላም ይህን አስደንጋጭ ነገር ተመልክቶ አዘነ ይህ ነገር ለእኔ የመጣ ነው ሁለት ነፍሳት በእኔ ምክንያት ሙተዋልና እኔም መሞት አለብኝብሎ ያንን የተበከለ መጠጥ ጠጥቶ ምንም ሳይጐዳው ቀረ ። በዚህ ምክንያት ንጉሡና ቢትወደዶቹ ሁሉ ጥላቻቸውን እያጠነከሩበት ይሔዱ ጀመር ቡሩኩ ላሊበላም ከሰው ጋር ከመቀመጥ ከዱር አራዊት ጋር መቀመጥ ይሻላል ብሎ ወደሌላ አውራጃ ሔዶ ተቀምጦ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ በራእዩ ተገልጾ የእግዚአብሔር ባለሟል ላሊበላ ሆይ ከአብራክህ የተመረጠ ልጅ ስለአለህ መስቀል ክብራ የምትባል ሴት ቅጠል ልትቀጥፍ ወደዚህ ነገ ትመጣለችና እርሷን አጭተህ አግባ ብሎት መልአኩ እንደነገረው ወደርሱ ስለመጣች እርሷን አጭቶ በሕግ በሥነ ሥርዓት በሽማግሎች መራቂነት አግብቶ ሳለ የሌለ ሰው የታጩችውን ሴት ልጅ አስገድዶ ያገባ ነው ብለው ከንጉሡ አቅርበው በሐሰት ምስክር የግርፋት ስቃይ ደርሶበታል ከዚያም በመልአኩ መሪነት አክሱም እንደደረሰ እርሷን አደራ ሰጥቶ በግብፅና በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቅዱሳት መካናትን ለመሳለም በቅቶ ፈጣሪው ክርስቶስ ተገልጾ ብዙ የምህረት ቃል ኪዳን ከነገረው በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የመንግሥትን ሥልጣን ከወንድሙ ተቀብሎ በኢየሩሳሌም የሚገኙት ቅዱሳት መካናት በሀገሩ እንዲገኙ ከቋጥኝ ድንጋይ ላይ 11 ቤተ መቅደሶች ፈልፍሎና ቦርቡሮ እንደሚያንጽ ዝርዝር ቤተ መቅደሶቹ ሳይታነጹ ቁልጭ አድርጐ ስለአሳየው እንደእንቦሳ እየዘለለ ለእግዚአብሔር ምስጋና አቀረበ ከዚያም ወደ ሀገሩ እንደተመለሰ ከመስቀል ክብራ ጋር ሁኖ ወደላስታ ሮሃ ጉዞውን ቀጥሎ ምድረሳይ ከምትባል ቦታ ላይ ውሃ ፈልቆለት አደረ በዚህችም ሌሊት ክርስቶስ ለንጉሡ ሀርቤ በሕልሙ ተገልጾ በወንድሙ ላሊበላ ላይ የፈጸመውን ግፍና በደል እያስታወሰ ከወቀሰው በኋላ የመንግሥቱን ሥልጣን ለላሊበላ እንዲያስረክበው ስመ መንግሥቱንም ገብረ መስቀል ብሎ እንደሰየመው በመንገዱ ላይም እንዳለሂዶ እንዲቀበለውና ሥርዓተ መንግሥት ሠርቶ ዕለቱን እንዲያነግሠው ስለነገረው ሠራዊቱን አስከትሎ በእግሩ ተጉዞ ላሊበላ ከደረሰበት ቦታ ላይ ተገናኝቶ ይቅርታ ጠይቆ በክብር ተቀብሎ ሮሃ ቤተ መንግሥት እንደደረሱ ንጉሡ ዕለቱን ሥርዓተ መንግሥት ሠርቶ በ1ሺ

ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የጋብቻ ኃላፊነት የነማን ነው?

በሀገራችን ባህልና ልማድ መሠረት ይህ የያዝነው ወር የጋብቻ ወራት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ። ይህም የ ሆነበት ምክንያት አብዛኛው የኢትዮ ጵያ ሕዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሞ ያ ስለሆነ በዚህ ወር ዝናቡ ያባራል ጐርፉ ይደርቃል እህልም ተወቅቶ በጎ ዳርና በታህሣሥ ወር ይገባል ። በዚህን ጊዜ ወላጆች ለልጆቻቸው በሃላፊነታቸ ው የመረጡላቸውን ይድራሉ ። በዝናቡ ና በጐርፉ ምክንያት ተለያይተው የከረ ሙት ቤተሰቦችም በሠርጉ ሳቢያ ይገና ኛሉ ወሩም የደስታና የፈንጠዝያ ወር መሆኑ የሚጠቆም በተለያየ ቋንቋና ዜማ ሲዘፈን በመሠማቱ ነው ።

አዎን ይህ ልማድና ባህል ተገቢውን ቦታ የያዘና ለሁሉም አመች ጊዜ በመሆ ኑ አሁንም ቢሆን በአገር ቤትም ሆነ በ ከተማ በሥራ እየተገለጸ ይገኛል ። ይህ ም የሚመሰገን እንጂ የሚነቀፍ አይመ ስለንም ነገር ግን ወደ ዋናው ዓላማችን እንመለስና የቀድሞ ጊዜ ጋብቻ ከላይ እንደገለጽነው ሃላፊነቱ የወላጆች እን ደነበር ግልጽ ነው ። በአሁኑ ጊዜስ የጋ ብቻ ሃላፊነት የማነው ? ብለን ብንጠይ ቅ ሁሉም እንደየስሜቱ መልስ ለመስ ጠት ይችላል ። ቢሆንም በአሁኑ አም ዳችን የራሳችንን አስተያየት እንገልጽ ላችኋለን ።

1ኛ የጋብቻ ሃላፊነት በቅድሚያ የሚ መለከተው ሁለቱን ተጋቢዎች ነው አንድ ወይም አንዲት ወጣት ትዳር ለ መመሥረት ሲፈልጉ በመጀመሪያ ማ ወቅ ያለባቸው ጥሩ ትዳር ሊመሠረት የሚችለው በክርስቶስ ፈቃድ የተመ ሠረተ መሆኑን አምነው ልቦናቸውን በ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር አቅርበው መጠየቅ እንዳለባቸው ነው ። ተጋቢዎ ች ጠባይ ለጠባይ መተዋወቅና ስለ ጉዳ ዩም በሚገባ ማሰብ አለባቸው ዓላማቸ ውም ዘላቂ የፍቅር ፣ የወዳጅነት ፣ የአን ድነትና የሕይወት መሆኑን በደንብ መ ረዳት አለባቸው ። ከዚያም በኋላ ተጋቢ ዎች በሚገባ ተዋውቀውና ተጠናንተ ው በመካከላቸውም የማይግባቡበት ነ ገር ካለ ከመጋባታቸው በፊት ካስወገዱ በኋላ ቢጋቡ ጥሩ ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ ።

ነገር ግን ጋብቻን ያህል ቁም ነገር በ ችኮላ ያለጥናት የተፈጸመ እንደሆነ ው ጤቱ እያደረ ሃዘን ስለሚሆን ተጋቢዎ ች በቅድሚያ እንዲያስቡበት ያስፈል ጋል ። በጋብቻ ምክንያት እስከ ሕይወ ት ፍጻሜአቸው ድረስ የሚያቆራኟቸ ውን ሰዎች የፍቅር ስሜትና የእያንዳን ዱ የጠባይ እድገት መመዘን አለባቸው የጋብቻን አንድነት ለመመሥረት የሚ ወሰደው እርምጃ ሁሉ በእውነተኛነት በታማኝነትና ባለማስመሰል መሆን አ ለበት ጋብቻ የአሁኑንም ሆነ የኋለኛው ን ሕይወት የሚነካ ነገር ስለሆነ ቁንጅ ናን ብቻ ተመልክቶ መፈጸሙ ከማይወ ጡበት ማጥ ውስጥ እንደ መዘፈቅ ይቆ ጠራል ።

2ኛ የጋብቻ ኃላፊነት የወላጆችም ነው፡- ምክንያቱም ወላጆች በልጆቻቸ ው ስቃይ አብረው ተሰቃይተው በደስ ታቸውም ተደስተው ያሳደጉ ስለሆነ አ ሁን በአንዳንድ ቦታ ሲደረግ እንደምና የው ልጆች የጋብቻቸውን ውሳኔ ሲያደ ርጉ እነርሱን ማግለሉ ተገቢ አይመስለ ንም ወላጆች ልጆቻቸውን ሙሉ በሙ ሉ በእኛ ሃሳብ ባትመሩም ምክራችንን ሰምታችሁ የሚጠቅማችሁን ምረጡ ሲሉ ልጆችም እግዚአብሔርን ከሚፈሩ ወላጆች ጋር በመመካከር ተስፋቸውን ና እቅዳቸውን ሁሉ ቢገልጹላቸው በሕ ይወት ልምምድ ካገኙት ትምህርት ያስ ረዱአቸዋል ይነግሩአቸዋልም ። ወጣ ቶች ይህንን ቢፈጽሙ ከብዙ ችግር ሊ ድኑ ይችላሉ ።

ስለዚህ የወላጆችን ምክር ችላ ማለቱ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል እንላለን ።

3ኛ/ ቤተ ክርስቲያንም ከጋብቻ ኃላ ፊዎች አንዷ ናት

የቤተ ክርስቲያንን ጊዜያዊ ዝግጅቷ ንና ጥሩ ሕንፃ ስላላት የፎቶግራፍ ማስ ቀመጫቸው ማሳመሪያ እንዲሆን በማ ለት ጋብቻቸውን ጥሩ ሕንፃ ባላቸው አ ብያተ ክርስቲያናት እየመረጡ የሚፈ ጽሙ ተጋቢዎች ጥቂቶች አይደሉም ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቱ አፈጻ ጸም ትክክለኛ አቀጣጫውን እንዲይዝ ልታስብበት ይገባል ። አማኞቿን በደን ብ ማስተማር ሲገባት በወቅቱ ፈልጋ ስ ላላስተማረቻቸው እነርሱም በገዛ ቤታ ቸው እንግዶች ሊሆኑ ይችላሉ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን እያንዳንዱ አማኝ ጥሩ የሞራል ይዞታና እውነተኛ የክርስቲያን አኗኗር እንዲኖር ማድረግ የቤተ ክርስቲያን ሃላፊነት በሆነ ነበር ስ ለሆነም ወጣቶች የሰው ሁሉ መሠረት የሆነውን ጋብቻ ሲመሠርቱ ቤተ ክርስ ቲያን ዝም ብላ መመልከት አይኖርባት ም ቤተ ክርስቲያን ልጆቿ ከእርሷ ከመ ራቃቸው በፊት ስለ ክርስትና እምነታ ቸውም ሆነ ስለ ጋብቻ ሥነ ሥርዓትማ ስተማር የሚያጠፋትንም ማረምና መ ቅጣት ሙሉ ሃላፊነት አለባት ።

ጋብቻ በጸሎት በእግዚአብሔር ፈቃ ድ የተመሠረተ ሰፊ ጥናትና መመካከር የተደረገበት እንዲሆን ስለሚያስፈልግ ወጣቶች ከመጋባታቸው በፊት ወደቤተ ክርስቲያን መጥተው ጠለቅ ያለ የጋብ ቻ ትምህርት እንዲወስዱ መጋበዝ ሃላ ፊነቷ ነው ። ተጋቢዎች ከመጋባታቸ ው በፊት የተዋወቁና ለቤተ ክርስቲያና ቸውም ማንነታቸውን በደንብ ለመግለ ጽ የሚችሉ መሆን አለባቸው እንጂ በጋ



የመጀመሪያው የጋብቻ መሠረት

ብቻቸው ጊዜ ብቻ በእግር በፈረስ ቁስ ፈልጉ ተብሎ ለጊዜው አንዱ ሻሽ የጠ መጠመ መስቀልንም የያዘ ተጉትቶ በ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስም አባት ሆኖ ቢፈ ርም ዋጋ አይኖረውም ። ስለዚህ እንዲ ህ ዓይነቱን ስህተት ሁሉ ቤተ ክርስቲ ያን እንድታርምና ኃላፊነቷን እንድታ ስከብር ይፈለግባታል ።

4ኛ/ የጋብቻ ኃላፊነት የኅብረተሰቡ ም ነው፡- ኅብረተሰብ ማለት የአንዲት ሀገር ሕዝብ ማለት ሲሆን የሕዝብ ኑሮ መሠረቱ የቤተሰብ ኑሮ ነው ። የቤተሰ ብም ኑሮ መሠረቱ ጋብቻ መሆኑ እሙ ን ነው ። ስለዚህ ጥሩ ኅብረተሰብ እንዲ መሠረት እያንዳንዱ ቤተሰብ ማሰብና በነገሩ መትጋት ይኖርበታል ።

ጋብቻ አሁን በጊዜአችን እንደምና የው ዛሬ ተጋብተው በመንፈቅ ገፋ ቢ ል በዓመት መፋታት ሳይሆን ጥሩ መሠረት ያለው ጋብቻ ሆኖ ለሀገሪቱ ጥሩ ቤተሰብ የሚመሠረትበት ኅብረተ ሰብ መሆን አለበት የጋብቻን ሥርዓት የማያከብር ሕዝብ ብርቱ ጤናማም ሕ ዝብ ለመሆን ከቶ ስለማይችል ኅብረተ ሰቡ አጥብቆ ማሰብ ግዴታው ነው ።

5ኛ/ የጋብቻ ኃላፊነት የሀገርም ጉዳ ይ ነው፡-አንዲት ሀገር ሀገር ተብላ የም ትጠራው የወንዟና የሸንተረሯ ግግር ብቻ ሳይሆን የሕዝቧም ሞራል ጠንካራ ነት ጭምር ነው ።

የአንድ ሀገር ሕዝብም ጥሩ ሊባል የሚችለው ሞራል ጠንካራና ሀገሩን እ ፍቃሪ ሃይማኖቱን አክባሪ ሲሆን ነው ። ይህም ሊሆን የሚችለው የጋብቻው መ ሠረት ጽኑ ሲሆን ነው ። ስለዚህም ይህ እንዲሆን ሀገሪቱ ጋብቻ እንዳይላላ ጠ በቅ ያለ ሕግ አውጥታ ችግሩ የሚወገ ድበትን ዘዴ መፍጠር ይኖርባታል ። ከ ዚህም ሌላ የኅብረተሰቡ ሞራል የሚወ ድቅበትን ማለትም በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ የመጠጥ ሰዓትን መቀነስ ብቻ ሳይ ሆን በጠቅላላ መጠጥ ቤቶችን መቀነስ ና ያልሆነ ተግባር የሚያስተምሩ ፊል ሞች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ማገ ድ የሀገሪቱ ኃላፊነት ነው ።

እንደዚሁም ከ18 ዓመት ዕድሜ በታ ች የሆኑ ወጣቶች ከመጠጥ ከሲጋራ ማ ጤስና ከመሳሰሉት ተግባሮች እንዲ ወገዱ ጥብቅ እርምጃና ቁጥጥር መውሰ ድ ግዴታ ያስፈልጋል ። ይህንንም በሥ ራ ለማሳየት በትምህርት ቤት የሚገኙ ት ወጣቶች ከነዚህ መጥፎ ድርጊቶች እንዲታገዱ መምከርና ማስተማር የሀገ ሪቱ ኃላፊነት ነው ። ይህ ከዚህ በላይ በ 5 ንዑሳን አርእስቶች ከፍለን ከሞላ ጐ ደል የዘረዘርነው ግዴታ ቢሟሉ መልካ ም ጋብቻ ሊመሠረት ይችላል ።

---

# ሰላም

ሰላም የደኅንነት ድልድይ የሕይወት መሠረት ነው ለማለት ይቻላል በዓለም ውስጥ ሰላም ከሌለ የሰው ልጅ ሕይወ ቱ ተጠብቆ መብቱም ተከብሮ ይኖራል ለማለት አያስደፍርም ።

የደስታም ምንጭ ሰላም መሆኑ ሥ ውር አይደለም ያለ ሰላም ደስታ አይገ ኝምና የመጀመሪያው ሰው በፈጸመው በደል ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔ ር መካከል የነበረው መንፈሳዊ ግንኙነ ት በመቋረጡ ሰላም ከገጸ ምድር ጠፍቶ ነበር በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ ለ ብዙ ሺህ ዓመታት በሚቆጠር ዘመን ተ ራርቆ ሲኖር የሰላም ባለቤት እግዚአብ ሔር በዓለም ላይ የነበረውን ችግር ለማ ስወገድና የሰውን መብት ለመጠበቅ ሰ ላምንም በዓለም ላይ ለመዘርጋት ቀደ ም ሲል "እድንሃለሁ" ብሎ ለመጀመ ሪያው ሰው የነገረውን ተስፋ ተግባራዊ ለማድረግ የሰማይ ርዝመትና የመሬት ስፋት የማይወስኑት አምላኩ በእመቤ ታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ማኅ ፀን ተወስኖ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነ ፍስን ነሥቶ በተወለደበት ወቅት መላ እክትና ሊቃነ መላእክት ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረቡት ምስጋና (ስብሐት ለእግ ዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር) ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ሉቃ.፪፥፲፬ ። የሚል ነበር ። ይህን አመለካከትና ከሊቃ ነ መላእክት የተሰጠውን የሰላም ምስጋ ና ስንመለከተው ሰላም የሚለው ድም ፅ ምን ያህል አስደሳች ዜና እንደሆነ እ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ቅዱስ ላሊበላ

ከገጽ ፲፩ የዞረ

161 ዓ'ም. ኅዳር 6 ቀን አነገሠው ቡሩኩ ጻድቅም እንደ ነገሠ ከመንግሥቱ ሕዝብ መካከል አዋቂና ብልህ የሆኑ 4 ሰዎች መርጦ ንቡረዕድ ርዕሰ ርውሳን ጋትርያርክ ሊቀ ካህናት እያለ በየክፍለ ሀገሩ ሾመ የሃይማኖት አባት የሚሆን አባ ገብርኤል የሚባል ጳጳስ ከእስክንድርያ አስመጣ የሕንፃ ሙያ ያላቸውን ከሀገሩ ሕዝብ መካከል አሰባስቦ ቤተ መቅደሶች የሚሠሩበትን ቦታ መካን ልዕልት ከምትባል ቦታ አጠገብ ቀይት ከምትባል ሴት በገንዘቡ ገዝቶ ፕላኑን እራሱ በማንሳት ለሠራተኞቹ የየዕለት ደመወዛቸውን በውል ተዋውሎ ቦታው በተፈ



ቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናቱን ሲሠራ የሚያሳይ ባሕላዊ ሥዕል

ጥሮ ቋጥኝ የሆነ ድንጋይ ቦታ ስለሆነለት ከላይ ወደታች እየቦረቦረ በሐረግና በመስቀል በማጌጥ 11 ቤተ መቅደሶች ከነቅጽራቸው በ22 ዓመት ውስጥ አንጾ እንደጨረሰ ቤተ ማርያም ቤተ መድኃኔዓለም ቤተ መስቀል ቤተ ደናግል ቤተ ሰንበት ቤተ ጐልጐታ ቤተ አማኑኤል ቤተ ገብርኤል ቤተ መርቆሬዎስ ቤተ ሊባኖስ ቤተ ጊዮርጊስ እያለ ስም አወጣላቸው ዝነኛው ንጉሥ እነዚህን ቤተ መቅደሶች ሲሠራ ለግድግዳቸው ማገር ለምርጊታቸው ጭቃ ለምሰሶአቸው እንጨት ለዋልታቸው ገመድ ለከዳናቸው ሣር ለመስኮቶቻቸው ሳንቃ አላስፈለገውም ግድግዳቸው ምርጊታቸው ምሰሶአቸው ዋልታቸው ከዳናቸው መስኮቶቻቸው የድንጋይ ፍልፍል ነው ላሊበላ በዘመኑ ያነፃቸው ቤተ መቅደሶች ብዙዎች ናቸው ዝርዝር ታሪካቸውን ለመግለጽ ብዙ ገጾች ስለሚያስፈልግ ትቸዋለሁ ገናናው ጻድቅ እነዚህን ቤተ መቅደሶች ሲያንጽና መላ ዘመኑን ሲኖር ጓትጓት ጉርሻ ቂጣ ከጐመን ጋር አንዳንድ ጽዋ ውሃ ብቻ እየተመገበ በውስጥ ማቅ ለብሶ በጾም በጸሎት ተወስኖ ሕዝቡን በትክክል እየመራ በፍቅር በሰላም ኖረ እንጅ የግፍና የጭካኔ ሥራ ሠራ የሚል ታሪክ አይገኝም ኖብያን ፤ ኬንያን ፤ የመንን በኢትዮጵያ ሥር ለመምራት የቻለውም አገሩን ለማስፋት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ቤተ መቅደሶቹንም ግብፃውያን አነፁለት እየተባለ ይወራ እንጅ እውነተኛ ወሬ አይደለም ስመ ጥሩው ላሊበላም በነዚህ ቤተ መቅደሶች ስፍር ቁጥር የሌለው የምህረት ቃል ኪዳን ከፈጣሪው ጋር በጸሎት ተገናኝቶ ተቀብሎ ለቤተ መቅደሶቹ አገልጋዮች ብዙ ካህናትን ክርስትጉልት ጋር በደንብሠርቶ የመንግሥቱን ሥልጣን ከአብራኩለተ



የታሪኩ አቅራቢ እኚህ ናቸው

ወለደው ልጅ ለይትባረክ እንዳይሰጠው ሕፃን ስለሆነበት ለትልቅ ወንድሙ ልጅ ለነአኩቶ ለአብ አስረክቦ በቤተ ማርያም ቤተ መቅደሱ ውስጥ በጸሎት ላይ እንዳለ በነገሠ በ40ዓመቱ በተወለደ በ70 ዓመቱ በ1212 ዓ.ም ሰኔ 12 ቀን አርፎ በቤተ ጐልጐታ ቤተ መቅደሱ ውስጥ በክብር ተቀበረ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ደግ ንጉሥ የቅድስናውን ሥራ መርምራና አጥንታ ቅዱስ የሚያሰኘውን የክብር ስም ሰጥታ የተወለደበትን ታኅሣሥ 29 ቀን የአረፈበትን ሰኔ 12 ቀን በየዓመቱ ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም



## ዜና ሊቃውንት

### ንቡረዕድ ገብረሥላሴ ጸሐፌ ትዕዛዙ ለዳግማዊ ምኒልክ

በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት የጽሕፈት ሚኒስትርነት መዓርግ ጋር የአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ንቡረ ዕድነት ሹመት ተሰጥቶአቸው የነበሩት ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በ1837 ዓ.ም. ከአቶ ወልደአረጋዊና ከወይዘሮ ወለተ ጊዮርጊስ በደብረ ብርሃን አካባቢ ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ሲፈቅድላቸውም በአንኮበር ከተማ አስቀድሞ የንባብ ቀጥሎም የዜማ የቅኔና የትርጓሜ ሐዲሳት ትምህርታቸውን ተራ በተራ ተማሩ ።

በቅኔና በሥነ ጽሑፍ ሞያቸውም እጅግ የሚመሰገኑ ታላቅ ሊቅ ስለነበሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የኢትዮጵያ ሊቃውንትንቅኔ ሰብስበው እንዲያሳትሙ ያነቃቁና ያተጉ መመሪያውንም የሰጡ መሆናቸውን የታሪክ ዘገባዎች ያረጋግጣሉ ።

በዚሁም በታተመው የቅኔ መጽሐፍ ውስጥ በእሳቸው በራሳቸው የተቀነባበሩት ልዩ ልዩ ቅኔዎች በከፍተኛ ሊቅነት መድረክ ላይ የቆሙ ለመሆናቸው ማረጋገጫዎች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ ።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በቤተ ክህነትም ሆነ በመንግሥት በኩል የተባበረ አገልግሎት ለማበርከት በነበራቸ ፍላጐት መሠረት በመጀመሪያ ለወይዘሮ ባፌና ልዩ ጸሐፊ ሆነው የቅንነትና የታማኝነት ሥራቸውን ቀጠሉ ።

በኋላም አለቃ ወልደ መድኅን ይባሉ የነበሩት የዳግማዊ ምኒልክ ጸሐፌ ትእዛዝ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በ1864 ዓ.ም "ጸሐፌ ትእዛዝ" ተብለው ተሾሙና የቤተ ክርስቲያንን ሊቃውንት ወደ ቤተ መንግሥት ለማቃረብና ቁልፍ ቁልፍ የሆኑትን ከፍተኛ ቦታዎች ለማስያዝ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኑ ።

ይኸውም በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ሥራ አብዛኛውን የሚካሄደው በኢትዮጵያ ሊቃውንት ስለሆነ ነው ።

የትምህርት ሚኒስቴር በመሆን በመላ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ትምህርት እንዲሰጥ ፤ የፍርድ ሚኒስቴርነቱንም ሥልጣን በሥራ በመተርጐም በከፍተኛ የነፍስ ግዳይ ወንጀል ላይ እንኳ ሳይቀር "ይሞታል አያስሞተውም " ብላ የመጨረሻውን ፍርድ እንዲጸድቅ በማድረግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ መንግሥት ታላቅ የሥራ ድርሻ በይበልጥ ለማበርከት የቻለችው በጽሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የሥራ ዘመን እንደሆነ ይነገራል ።

ጸሐፌ ትእዛዝ የተመራመረ ፤ የተማረና በአስተያየቱ የበሰለ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ካጋጠማቸው ለዚያ ምሑር ቀለብ ደመወዝ ሳያስወስኑ ፤ ወይም ተገቢውን ሹመት ሳያሰጡ በፍጹም እንቅልፍ እይወስዳቸውም ነበር የሚሉ ብዙዎች ናቸው ፤ ይሁን እንጂ ለሹመት የሚያጩትን እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ሊቅ በጠባይ ይዘቱ በኩል ምን ዓይነት አቋም እንዳለው የማጥናቱንና የመከታተሉን ጉዳይ ቅድሚያ ይሰጡት እንደነበረ ይነገራል ።

ይኸውም ዛሬ ሾሞ ነገ መሻሩን እየተሳቀቁትና እንደነውርም እየቆጠሩት መሆኑ ይተረካል ፤ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ በጸሐፌ ትእዛዝነቱ መዓርግ ለሰላሣ ስድስት ዓመት ያህል በትጋት ፤ በቅንነትና በታማኝነት ሲሠሩበት ከኖሩ በኋላ ያበረከቱት የአገልግሎት አስተዋጽኦ ተገምግሞ በ1900 ዓመተ ምሕረት ለመጀመሪያ ጊዜ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የሚኒስትርነት ሹመት ሲጀመር በዚያው አስቀድሞ ይዘውት በነበረው ሥራቸው የኢትዮጵያ መንግሥት የጽሕፈት ሚኒስቴር የሚያሰኝ ከፍተኛ መዓርግ አገኙ ።

በዚህም ወቅት የእንጦጦ ደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤልን አስተዳዳሪነት በተጨማሪ ተሾመው ደብሩን በሚገባ አስተዳደሩ ።

ከዚህም ቀደም ብሎ በ1894 ዓ.ም ዳግማዊ ምኒልክ የአዲስ ዓለም ዳግማዊት ጽዮንን ቤተ ክርስቲያን በሚገባ አሳንፀው ሥርዓቷንም ሆነ መዓርጓን በአክሱም ትይዩ አድርገው የንቡረዕድነቱን ሹመት ለማን እንደሚሰጡት በሰፊው ያመዛዝኑ ነበር ።

በመሆኑም መኳንንቱ ሊቃውንቱ ለዚህ ሹመት ተገቢ የሆነውን ሰው በስብሰባ መርጠው እንዲያቀርቡላቸው ትእዛዝ ሰጡ ። የሚመረጠውም ሰው ባለሙዋልነትን ከትምህርት ጋር አጣምሮ የያዘ መሆን እንደሚገባው አስገነዘቡ ማለት መመሪያ ሰጡ ፤ ይህ ለምን እንዳስፈለገ ሲያስረዱ "'በባለሟልነቱ ይህ ቀረ ፤ ያጐደለ ፤ እንዲህ እንዲህ ያለው ያስፈልጋል ብሎ ደፍሮ እንዲያስታውሰኝ ፤ በትምህርቱ ካህናቱንም ሆነ ምእመናኑን በዕውቀት በምርምር እንዲያንፅ መናፍቃንን እንዲገሥፅ ነው ።"አሉ ይኸንኑ መመሪያ የተቀበሉት መኳንንትና ሊቃውንትም የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልንና አሁን መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ የተባለውን የቀድሞውን የመካነ ሥላሴን አድባራት በየተራ የተሾሙትን ታላቁን ሊቅ አለቃ ወልደ ማርያምን በተባበረ ድምፅ መርጠው አሳባቸውን አቀረቡ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፤ በባለሙዋልነትም ሆነ በትምህርት የተሟላ ይዘት ያላቸው አለቃ ወልደ ማርያም ለአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ንቡረ ዕድ ቢሆኑ ተገቢ መሆናቸውን አምነውበት ለኒሁ ለአዲሱ ተሿሚ የራስ ወርቅ የወርቅ ሜዳ



www.ethiopianorthodox.org

የወርቅ ላንቃ የወርቅ መቋሚያና የወርቅ ጸናጽል የወርቅ ወንበር በአስቸኳይ ተዘጋጅቶ ንቡረዕድነቱ እንዲሰጣቸው አዘዙ ።

በዚህም ወቅት ለዳግማዊ ምኒልክ አንድ ነገር ትዝ አላቸው ይኸውም የቤተ ክህነቱን ሥርዓት በሚገባ አድርገው ጠንቅቀው የሚያውቁትና በአሳብ ሰጭነት ችሎታቸውም ተደማጭነት የነበራቸው የአፈ ንጉሥ እስጢፋኖስ በጉባኤው አለመገኘት ነበር ።

በመሆኑም አፈ ንጉሡን ወዲያውኑ አስጠርተው የጥናቱንና የውሳኔውን ሁኔታ ቢያስረዷቸው አሳቡን ማለት የሊቁን ተፈላጊነትና ተገቢነት ሙሉ በሙሉ አረጋገጡ ።

ብቻ አሉ "አፈንጉሥ እስጢፋኖስ ንቡረዕዱ በታላላቅ በዓላት የወርቅ ጫማ መጫማት አለበት ስለዚህ የሊቁ እንድ እግራቸው በሽተኛ ነውና ያስቸግር ይመስላል አሉ"

በዚህም ወቅት በአዲስ ዓለም ዳግማዊት ጽዮን ደብር ምንም ዓይነት ነቀፌታን ያስከተለ ነጥብ እንዲገኝ የማይፈልጉት ዳግማዊ ምኒልክ ከቀሩት መማክርት ያመለጠው አሳብ ከአፈ ንጉሥ በመገኘቱ እጅግ አድርገው አደነቁና የአለቃ ወልደ ማርያምን ሹመት በዚሁ ብቻ ውድቅ አድርገው የተደከመበትን አሳብና ጥናት ማፍረስ ብቻ ሳይሆን እንደገና ሌላ አዲስ ሕንፃ ማነጽ ያስፈልግ ሃልና አንተ በበኩልህ ማን ቢሆን ይሻላል ትላለህ "? ብለው አፈ ንጉሡን ስለ ጠየቁዋቸው እንደእኔማ ቢሆን በአንድ በኩል የተማረ ሊቅ በሌላ በኩል ደግሞ በቅርብ የሚያውቁትና ጠባዩን የመረመሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ስለ ሆን በዚሁ በያዘው ሹመት ላይ ንቡረዕድነቱ ቢፈቀድለት ደስ ይለኛል ሲሉ አሳብ ሰጡ ።

በዚህ አሳብ ላይ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ለመሰንዘር ያልፈለጉት ዳግማዊ ምኒልክም ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የክብር ልብሱን ለብሰው የወርቁን ጫማ ተጫምተውና የራስ ወርቁን ደፍተው እንዲቀርቡ መኳንንቱና ሊቃውንቱም እንዲሰበሰቡ ወዲያውኑ አዘዙ ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የተዘጋጀውን የክብር ልብስ ለብሰውና ሹመቱ ተነግሯቸው እጅ ለመንሣት ሲቀርቡ ዳግማዊ ምኒልክ ፡ ገብረሥላሴ!! "የመረጥኩህ እኔ አይደለሁም ፤ የመረጡህ ቅንነትህ ፤ ታማኝነትህና ፤ አገልግሎትህ ተባብረው ነው ፡ እኔ አስተናባሪ አዳይ እንጂ ሰጭው እግዚአብሔር ነው ስለአሉዋቸው በዚህ አነጋገር ልባቸው የተነካው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እያለቀሱ "ከአቧራ ላይ አንሥተው ሰው ቢያደርጉኝ ሰው ሆንኩእንጂ ለርስዎ ስጦታ የኔ ታማኝነትና አገልግሎት ምኑ ነው በማለት ዕንባቸው አልታገድ አለ።

በዚህም ወቅት ፈሊጠኛው አፈንጉሥ እስጢፋኖስ "ሲሾሙህ ያለቀስክ ቢሽሩህ ምን ልትል ነው "? ብለው ሁሉንም ስለአሳቁት የጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ኃዘን ተለውጦ ኃዘኑም ለጊዜው ፀጥ አለና በቤተ መንግሥቱ እንዲሁም በተሿሚው መኖሪያ ቤት የደስታ መግለጫ ተደረገ ።

ንቡረዕድ ገብረሥላሴ ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ ከጥቂት ቀን በኋላ በብዙዎች ሊቃውንትና መኳንንት ታጅበው በዘመኑ የትራንስፖርት አገልግሎትን ይሰጥ በነበረው ሠረገላ ከባለቤታቸው ጋር ሆነው አዲስ ዓለም ዳግማዊት ደብረ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ጥንግ ድርብ ባለወርቅ ካባ ቀሚስ ለብሰው የብር መቋሚያና ጸናጽል ይዘው የሚጠባበቁት ሊቃውንት ካህናት በይባቤ ተቀበሉዋቸው ።

የባለቤታቸውም ስም "ወይዘሮ ዕሜቴ" ስለነበረ ሊቃውንቱ ይኸንኑ ሁኔታ በማስመልከትና ምሥጢሩን ከምሥጢር በማስተባበር "ዘዕሜቴ ምስሌሁ ወምግባሩ ቅድመገጹ ገብረ ሥላሴ ጸሐፌ ትእዛዙ ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሥ ኪ ጽዮን ጻድቅ ወየዋህ ምኒልክ" ኃሚል ግሥ ገሥሠው እንዳለ ዘቡና በዚሁም በጣም እንደተመሰገኑበት ይነገራል ።

በዚህም ወቅት አዲስ ዓለም እንደስሟ በእውነቱ አዲስ ዓለም ሆነች ፤ የብሉያት ፤ የሐዲሳት የሊቃውንት ትርጓሜ የዜማ የቅኔ መምህራን ሊቃውንት እጥፍ እየሆኑ በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ጉባኤ ዘርግተው እንዲያስተምሩ አደረጉ ።

በዚህ ጊዜ ነበር የታወቁት የሐዲስ መምህርና እውነተኛው አርበኛ መምህር ወልደ ሚካኤል በአዲስ ዓለም ደብረ ጽዮን ጉባኤ ዘርግተው ትርጓሜ ሐዲሳትን ያስተምሩ የነበረው ።

የብሉዩና የቅኔው መምህር ስመ ጥሩው አለቃ ተጠምቆም በዚሁ ደብር ጉባኤ ዘርግተው ያስተምሩ ነበር ።

ጸሐፌ ትእዛዝ በትምህርትና በመልካም ጠባይ የተማመኗቸውን ሊቃውንት በተከታታይ በአዲስ ዓለም ፤ በእንጦጦ ራጉኤል በሌሎቹም ታላላቅ አድባራት ሁሉ በመመደባቸው ፤ ይልቁንም በጐንደር በጐጃም ፤ በሸዋ ፤ የሚገኙትን ሊቃውንት ደጅ ሳይጠኑ ራሳቸው ካሉባት እያስፈለጉ በገዳማት ፤ በአድባራት እንዲሾሙ የተወሰነ መተዳደሪያ እየተሰጣቸው እንዲያስተምሩ በማድረጋቸው ከፍ ያለውን መንፈሳዊ ዝና ለማትረፍ ቻሉ ።

የአዲስ ዓለምን የግል ቤታቸውን ከቤተ ልሔም ላስመጧቸው ለመዝገበ ድጓው መምህር ለሊቀ ጉባኤ ቴዎድሮስ ሰጡ የመኖሪያ ቤታቸው ማዕድ በሊቃውንት ብቻ የተከበበ በመሆኑ ምግቡ ተጀምሮ ገበታው ከፍ እስኪል ድረስ ከሊቃውንቱ ጋር ስለ ምሥጢረ መጻሕፍት ምሥጢር ከመነጋገርና አሳብ ለአሳብ ከመለዋወጥ በቀር ሌላ ዓለማዊ ነገር አይነገርም ነበር እየተባለ ይተረካል ።

ንቡረዕድ ገብረ ሥላሴ ዘውእቱ ጸሐፌ ትእዛዝ ሠርቶ በማሠራት የሥራን ክቡርነትም ዐውቆ በማሳወቅ በጣም የተመሰገኑ እንደነበሩም ታሪክ ያረጋግጣል ።

ለምሳሌም አንድ የግል ጸሐፊያቸው ሆኖ በቤታቸው የሚኖር ሠራተኛ ለሥራ እየፈለጉት ሊያገኙት ስለአልቻሉ ከመገሠፅም ሆነ በገንዘብ ከመቅጣት የተሻለ መስሎ የታያቸውን ልዩ ዘዴ መረጡ ይኸውም ቀጥሎ የተመለከተው ነው

አንድ ባዶ የሆነ አንቬሎፕ አሽገው ጧት ከቤታቸው ወደቤተ መንግሥት በበቅሎ ሲሔዱ ይኸንን ከዚያው ከግቢ ስደርስ ትሰጠኛለህና ይዘህ ተከተለኝ ብለውት ከቤተ መንግሥት ደርሰው ከበቅሎ ሲወርዱ ቢሰጣቸው ወደቤት ስንመለስ ትሰጠኛለህ አሉት ።

በዚህም ዓይነት ከቤት ሲሰጣቸው ከቤተ መንግሥት ፤ ከቤተ መንግሥት ሲሰጣቸው ከቤት እያሉ ለአሥራ አምስት ቀን ያህል እንዳይለያቸው አደረጉ ከዚህ በኋላ ግን እየወተወተ ስለአስቸገራቸው ለልዩ ጸሐፊያቸው እንዲሰጠው አዘዙት ።

ልዩ ጸሐፊውም ተቀብሎ ቢከፍተው ባዶ ኤንቬሎፕ ሆኖ ስለአገኘው የሰጠውን ጸሐፊ ከሥራህ ላይ እየታጣህ ስለ አስቸገርከ በዘዴ ትምህርት ሲሰጡህ ነውና ለወደፊቱ ተጠንቀቅ ብሎ መከረው ጸሐፊውም ሁኔታውን ስለተረዳው የሥራን ክቡርነት ዐውቆ ጠባዩን ሊያሻሽል እንደቻለ ይነገራል ።

ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ "ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ" ተብሎ በ1959 ዓ.ም የታተመውን መጽሐፍ ቀደም ብለው ረቂቁን አደራጅተው በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት እንዲቀመጥ አድርገው እንደነበረ ይኸው መጽሐፍ ያስረዳል ።

ስለዚህ ንቡረዕድ ገብረሥላሴ ዘውእቱ ጸሐፊ ትእዛዝ በዚህና ከላይም በተዘረዘረው ሁሉ ለኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ባለውለታ ናቸው ለማለት ይቻላል ።

ይኸንንና ይኸንን በመሳሰለው ሁኔታ ሕይወታቸውን በታሪክና በሥራ ሲያስጌጡ ከኖሩ በኋላ ጥቅምት 27 ቀን 1905 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ባቀኑት ባፀኑትና ባስተዳደሩት በእንጦጦ ራጉኤል ደብር ተቀበሩ ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

## የደም ብዛት መከላከያ

ደም በሰውነታችን ውስጥ ያለ አስፈላጊ የሆነ ፈሳሽ ነው ። የሰው ልጅ ሕይወት እንዲኖረው ደም በሰውነት ውስጥ መዘዋወር አለበት ። የደም ብዛት ሲባል አንዳንዶቻችን ደም በሰውነታችን መጠኑ ከተወሰነ በላይ በዝቶ ሊፈስስ የደረሰ ይመስለን ይሆናል ። አይደለም የደም ብዛት የተባለው የደም ሥር በሽታ ሲሆን በሰውነታችን ውስጥ ያሉት የደም ቧንቧዎች ካላቸው የስፋት መጠን በመጥበብ የደም ግፊቱ እንዲጨምር ያደርጋሉ ። ይህም ግፊት በማያቋርጥ ሁኔታ ሲዘዋወር በሰውነታችን ላይ ጠንቅ ሊያስከትል ይችላል ። የደም ግፊት ሊለካ የሚችልበት መሣሪያ አለ፡ ይኸውም ልባችን ሁለት ክፍሎች አሉት የታችኛው የልብ ክፍል እና የላይኛው የልብ ክፍል በመባል ይታወቃሉ ። ይህ መሣሪያ የልባችን የታችኛውን ክፍል በሚጨበጥበት ጊዜ ትክክለኛው የደም ግፊት 140 ሚ.ሜ. ከፍታ ላይ ያሳያል ። ከዚህ በላይ የሆነ ግን የደም ብዛት እንዳለው ያረጋግጣል እንደገና ደግሞ የተጨበጠው የልባችን የታችኛውክፍል በሚዘጋበት ጊዜ በትክክለኛው የሚያሳየው 90 ሚ.ሜ. ከፍታ ሲሆን ከዚህ በላይ ከሆነ ግን አሁንም የደም ብዛት እንዳለው ያሳያል ማለት ነው ። የደም ብዛት ለልብ ድካም እንዲሁም ለኩላሊት ድክመት ምክንያት ሊሆን ይችላል ደም በሰውነታችን ክፍል በሚገኙት የደም ቧንቧዎች ግፊቱን እንዲጨምር ወይም ደግሞ የደም ቧንቧዎች እንዲጠቡ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ ። ከዚህም

1 መበሳጨት ፡ የአእምሮ ጭንቀት፡ (መነጫነጭ)

2 ቡና በብዛት መጠጣት

3. ሲጋራ ማጨስ ፡ አልኮል መጠጦችን ማብዛት ፡

4. ስባት ነክ ምግቦችን ማብዛትና የሰውነት ውፍረት ከተወሰነ በላይ ሲጨምር እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የደም ግፊትን ከተወሰነ በላይ በመጨመር ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ ። አንድ የደም ብዛት ያለበት ህመምተኛ የደም ግፊቱ ቶሎ ቶሎ መለካት አለበት ። ምክንያቱም አስፈላጊውን እርዳታ ለመስጠትና የሰውየውን ሁኔታ ለመገምገም እንዲያመች ነው ። የደም ብዛት በሁለት ይከፈላል ። ምክንያቱ የሚታወቅና ምክንያቱ የማይታወቅ በመባል ይታወቃል ። ይኸውም በግምት ከ90 % ሕዝብ በላይ የሚሆነው ምክንያቱ የማይታወቅ ሲሆን ሌላው ደግሞ ምክንያቱ የሚታወቅ ነው ።

የደም ብዛት አንደኛው ክፍል ቤተሰባዊ ነው ይኸም ማለት ከዘር ተያይዞ ሊመጣ ይችላል ። ይህ ከዘር የሚመጣው በሽታ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑም በላይ በብዛት የሚያጠቃው ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን ነው ። ይህ በሽታ ለረጅም ጊዜ የቆየባቸው ሰዎች በሰውነታቸው ውስጥ በሚገኙት የደም ቧንቧዎች ላይ ከፍተኛ አደጋ በመጣል ጠቅላላ የሰውነትን ክፍል በጣም ይጐዳሉ ። በይበልጥም በዐይን ፤ በልብ ፡ በኩላሊትና በአንጐል ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ። ይኸውም የማየት ኃይልን በመቀነስ ደምን ወደ ልብ እና ወደ ኩላሊት የሚወስዱትን የደም ቧንቧዎች በመዝጋት ደም እንዳይዘዋወር ያደርጋሉ ። በተጨማሪም ከላይ እንደተጠቀሰው ለልብ ድካም ምክንያት በመሆን ሰውነታችንን ሙሉ በሙሉ ጉዳት ላይ ሊጥሉ ይችላሉ የደም ብዛትን ለመከላከል በሀኪም ትዕዛዝ የምንጠቀምባቸው መድሐኒቶች አሉ እነሱም በሰውነታችን ውስጥ በገቡ ጊዜ የደም ቧንቧዎችን በማስፋት አእምሮን እንዳይጨነቅ እረፍት ይሰጣሉ የደም ብዛትን ከመድሐኒቶች ሌላ የምንከላከልበት ሌላ ዘዴ አለ ።

ይኸውም አንድ ሰው በሚበሳጭበት ጊዜ እና በሚጨነቅበት ጊዜ የደሙ


www.ethiopianorthodox.org

ግፊት ሲጨምር ይችላል ይህ እንዳይ
ሆን ሰውየው ማለትም ህመምተኛው
እንዲረሳው የተለያዩ ወሬዎችን ማው
ራት በአጠቃላይ ሰውየውን እንዲደ
ሰት ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

አንድ ሰው ስባት የበዛበትን ምግብ
ለምሳሌ እንቁላል የመሳሰሉትን ስባት
ነክ ምግቦች አዘውትሮ ከተመገበ ውፍ
ረቱ ከልክ ያለፈ ሊሆን ይችላል በዚህ
ጊዜ የደም ቧንቧዎች ይጠቡና የደም
ብዛት አይነተኛ ምክንያት ሊሆን ይች
ላል ስለዚህ ውፍረት ለመቀነስ ስባቶ
ችን መቀነስ አስፈላጊ ነው በተጨማ
ሪም ሲጋራ ማጨስ አልኮል መጠጦችን
ማብዛት የደም ብዛት ምክንያት ስለሚ
ሆን እነዚህንና የመሳሰሉትን በጭራሽ
ማስወገድ አለብን በተጨማሪም ለህመ
ምተኛው ትምህርት በመስጠትና ምክ
ር በመስጠት ስለ ግል ችግራቸው እንዳ
ይበሳጩና ጊዜያቸውን በተመቻቸ ሥራ
እና ዕረፍት በመውሰድ እንዲያሳልፉ
ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው ።

የደም ብዛት ሲይዝ በሰውነት ላይ
ብዙ የተለያዩ ምልክቶችን ያሳያሉ ።

1/ ጠዋት ጠዋት ከመኝታ ሲነሱ
ራስ ምታትና የድካም ስሜት ይሰማል።

2/ የልብ ህመምን በማከታተል በም
ንተነፍስበት ጊዜ ህመም ይሰማል ።

3/ እንዲሁም ደግሞ ሽንት በብዛት
ያሸናል

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምልክቶች
በሰውነት ላይ ከታዩ በሽተኛው ወዲያ
ውኑ ወደ ሐኪም ቤት በመሄድ የሐ
ኪም እርዳታ ማግኘት አለበት ። ህመ
ምተኛው የሚሰጠውን መድኃኒት በሰ
ዓቱና በታዘዘው መጠን መውሰድ ይኖ
ርበታል ። ይህ ከተጓደለ ግን የህመም
ተኛውን የደም ግፊት መቆጣጠር በጣ
ም አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ በልብ
ላይ ተጨማሪ አደጋ መጣል ነው ።

በተጨማሪም አንድ የደም ብዛት
ያለበት በሽተኛ ጨው ያለበትን ምግብ
መመገብ አይኖርበትም ። በዚህ ሁኔታ
የሀገራችን ሕዝብ አንድ ምግብ በሚቀ
ርብለት ጊዜ ጣዕሙን ሊወስንለት የሚ
ችለው የቅቤ ወይም የበርበሬ መኖር
ብቻ ሳይሆን የጨው መኖር ነው ።
ጨው የደም ብዛት ላለበት ህመምተኛ
አስፈላጊ ስላልሆነ የጨውን ምግብ መ
ቀነስ እጅግ አስፈላጊ ነው ።

ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠን
ቀቅ እንዲሉ ጨው ያለበትን ምግብ
ተመገቦ በበሽታ ከመሰቃየት ጨው
ያለበትን ምግብ ያለመብላትና በጤና
መኖሩ ይመረጣል ። ስለዚህ ይህንን
ሁሉ ለህመምተኛው መንገር አስፈ
ላጊ ነው ።

ለህመምተኛው ከዚህ የሚከተሉትን
ሦስት ምክሮች በመስጠት የደም ግፊት
እንዳይጨምር መከላከል እንደሚቻል
ማሳሰብ ተገቢ ነው ።

1/ አንድ የደም ብዛት ያለበት ሕመ
ምተኛ ወተትና የወተት ክፍሎችን አይ
ብን የመሳሰሉትን መጠጣት ወይም
መብላት አይኖርበትም ምክንያቱም
ላም በተፈጥሮ በወተቷ ውስጥ ጨው
አለ ስለዚህ ጨው ለደም ግፊት መጨ
መር ምክንያት ስለሆነ ህመምተኛው
መመገብ አይኖርበትም ።

2/ ለህመምተኛው ምግብ በሚሠራ
በት ጊዜ ጨው ፍጹም መግባት የለበት
ም ፤

3/ ህመምተኛው ፍራፍሬና ጥሚቂ
ዎችን መብላት ይኖርበታል ፤

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን አስፈ
ላጊ ምክሮች የመስጠት ጉዳይ የጤና
ባለሙያዎች በተለይም ነርሶችን የሚ
መለከት ነው በተጨማሪም ምክሩንና
ትምህርቱን ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋ
ሉ ደግሞ የህመምተኛው ፋንታ እንደ
ሆነ መታወቅ አለበት ።

ተማሪ ነርስ መንበረ ምህረቱ

---

# ሰላም

ከገጽ ፲፯ የዞረ

ንመለከታለን ባለንበት ምድራዊ ዓለም
ሰላም እንዲሰፍን የጥላቻ መንፈስ
እንዲጠፋ የዓለም ሕብረተሰብ ሁሉ ጥ
ረት ከማድረግ የተቆጠበበት ጊዜ እንደ
ሌለ ታሪክ ይመሰክራል ።

ነቢያትም ሆኑ ሐዋርያት ባጭር ታ
ጥቀው በጋለ መንፈስ ሕዝቡን እንዲያ
ስተምሩ ሕዝቡ በሰላማዊ መንገድ እን
ድሂድ ያደረጉት የነበረው ጥረት ስለ
ሰላም ነበር ።

ለምሳሌ ከደቂቀ ነቢያት አንዱ ነቢ
ዩ ዘካርያስ እውነትን ያዙ ሰላምንም ተ
ከተሉ (ውደዱ) እያለ ያስተምር ነበር
ዘካ.8፡19 ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ሰላም
ሲያስተምር ክርስቶስ "ሰላምን ያደርግ
ዘንድ ጥልን በመስቀሉ ገድሎ ርቃችሁ
ለነበራችሁና ቀርባችሁ ለነበራችሁ ሰ
ላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ» ብሏል ።
ኤፌ.፪.፲፯፡፲፯ ።

አርሚጦስ የተባለውም ፈላስፋ ለተ
ፈጥሮ ጠባይ ደግነት ጥንትና ፍጻሜ አ
ላት ይኸውም ጥንቷ መፋቀር ሲሆን ፍ
ጻሜዋም ሰላም ነው ብሏል ።

የዓለም ሕዝብ እስካሁን ድረስ ስለ
ሰላም ይወያያል ስለ ሰላምም እየተሰበ
ሰበ ይነጋገራል ይሁን እንጂ የሰላምን
ጉዳይ ከማንበብ በስተቀር ተተርጉሞ
ሲገለጽ አይታይም ።

ከዚህም የተነሣ ኃይል የሌላቸው ጥ
በብ የጎደለባቸውና ከዘመናዊው ሥል
ጣኔ ወደኋላ የቀሩት ሕብረተሰቦች ነፃ
ነትን እኩልነትን ትክክለኛ ፍትሕንና
ሰላምን በማጣት እረ የሰላም ያለህ እያሉ
የሚጮሁ በጥቂቱ የሚገመቱ አይደሉም
ይሁን እንጂ ደም እያለቀሱ ቢጮሁም
ሰሚ ጆሮ አላገኙም እንዲያውም
በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም እየታተ
መ ለሕዝብ የሚሰራጩ ጋዜጦችና መ
ጽሔቶች የሚያቀርቡትና ይዘውት የ
ሚታየው ዜና በሰው ላይ ያለውን ችግ
ር እንጂ የሰውን ደስታ ሲያበስሩ አይሰ
ሙም ጋዜጣው ቢያነቡት በእገሌ አገር
ይህን ያህል ሕዝብ አለቀ ይላል መጽሔ
ቱም ቢመለከቱት በአገሌ አገር ይህን
ያህል ሕዝብ በረሀብ ተሰደደ ይህንን ያ
ህል ሕዝብም መጠጊያ አጥቶ በችግር

ወደገጽ ፳፱ ዞሯል



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## 1 ሥርዓተ አንቀጽ

ደራሲው መጠነኛ ስፋት ያለውን አ
ንድ ፍሬ ሐሳብ የተሸከመ ኃይለቃል
ያለበትን የአንድ ዓይነት ሥረ-ወጥ አር
ቲክል ንዑስ ክፍል በአንድ ወይም በጥ
ቂት ዐረፍተ ነገሮች መግለጥ ካልቻለ በ
ቀር በአንቀጽ መከፈል (መለየት)ይኖር
በታል ። አንቀጽ ማለትም ተዛማጆች የ
ሆኑ ጥቂት ዐረፍተ ነገሮች ተረዳድተ
ው አንድን ፍሬ ሐሳብ ግልጥ ለማድረ
ግ የሚችሉበት የጥቂት ዐረፍተ ነገሮች
ስብስብ (ድምር ) ነው እርሱም በልሣነ
እንግልጣር ፓራግራፍ ተብሎ የሚጠራ
ው ነው ።

ከዚህም በተረፈ ዐረፍተ ነገሮችም
ሆኑ አንቀጾች በመርዝም እንዳይመዘ
መዝ አማራጭ የሌለው ዓይነተኛ ዘዴ
ቅጽሎችን፣መስተዋድድናመስተፃምር
ን ሐረጎችንና የመሳሰሉትንም ሁሉ አ
ለማብዛት ነው ታዲያ እነዚህ ሁሉ አያ
ስፈልጉም ለማለት ሳይሆን አገባባቸው
በመጠኑ እንዲሆን ጥንቃቄ ማስፈለጉን
ለመጠቆም ያህል ብቻ ነው ።

## 2. የድርሰት አከፋፈል

ጥራትና ዓላማ ያለው ማንኛውም ድ
ርሰት ወይም ንግግር በሦስት ይከፈላል
ይኸውም 1/ መግቢያ (ኢንትሮዳክሽን)
የሚባለው ነው ይህም ክፍል ማንኛን
ድርሰት ወይም የንግግር ርዕስ ከአንባብ
ያንና ከአድማጮች ጋር ለማስተዋወቅ
የሚያስችል መቃረቢያ ስለሆነ ጥንቃ
ቄን በተሞላ ሁኔታ መነደፍ ይኖርበታ
ል "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያ
ታወቃል " እንዲሉ አንባቢውም ሆነ
አድማጩ ወደፊት የሚቀጥለውን ም
ሉእ ሐተታ ውጤቱን በናፍቆት ወይም
በሰቂለ ኅሊና መጠባበቅ የሚችለው
ገና ከመግቢያው ላይ በሚገኘው ብሩህ
ተስፋ ሰጭ መግለጫ ነው ። ጥራትና ው
በቱ የሚለካውም ከዚህ ጀምሮ ነው ።

## 3. ሐተታ (ቦዲ ይሉታል)

ይህም ክፍል ዋናው የድርሰቱ ባሕረ
አሳብ (አካል) በምልአት የሚቀርብበ
ትና ፍሬ ሐሳብ የሚዳሰስበት ተነቦም
ሆነ ተሰምቶ ቅርፅና ይዘቱ ጥቅምና ጉ
ዳቱ ምርትና ገለባው ተለይቶ ደራሲው
ን ከማመስገንም ሆነ ከመንቀፍ ደረጃ
የሚያደርሰው ወሣኝ ነጥብ ያለበት ክ
ፍል ነው ።

## 4.መደምደሚያ(ኮንክሉሽን)

የተጻፈው ድርሰት ወይም የቀረበው
ንግግር ድስኩር ተመዛዝኖ ፍሬ ነገሩ ተ
ጨምቆ የነጠረ ማጠቃለያ ዝክረ ነገር
በማብሠር ማሰናበቻ ስለሆነ አጻጻፉ ብ
ርቱ ጥንቃቄ የተሞላ መሆን ይኖርበታ
ል ። ይህም የመደምደሚያ ሐሳብ በአን
ባቢዎች ወይም በአድማጮች አእምሮ
በማይረሣ ሁኔታ ተቀርፆ እንዲኖር ማ
ድረግ የሚያስችል መሆን አለበት ።

ስለዚህም ከዋናው ድርሰት ዋና ዋና
ዎቹን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ እጥ
ር ምጥን ባለ ሁኔታ ብጥር ንጥር አድር
ጎ የማስቀመጥ ችሎታ ይጠይቃል ።ዳሩ
ግን በቀጥታ ከለሳ ዓይነት መሆን የለበ
ትም ። ውበት ባለው የማጉልመሻ አገ
ላለጥ ፍሬ ነገሮችን በግልጥ ቋንቋ ለማ
ስጨበጥ እንጂ ደግሞ ቃል ከበዛበትማ
አንድን ድርሰት ወይም ንግግር ሁለት
ጊዜ እንደመጻፍ ይቆጠራል ። ባጠቃላ
ይ መደምደሚያ አቀራረብ ምርመራው
የሐተታውን የተመሰገኑ ደራስያን የ
ሚመሩበትን ዘዴ (ክራይቴርያ) መከተ
ል ይገባል ።

## 5.የድርሰት ሐሳብ መክፈያ

- የቅደም ተከተል ማስተካከያ

--- የኃይለ ቃላት ማጉልመሻ አንድ ጥ
ሩ ድርሰት እነዚህን ሦስት ነገሮች አስ
ተባብሮ ይዞ መገኘት አለበት ።

1/ መክፈያ፡-አንድ የተወሰነ ሐሳብ ከሌ
ላው ጋር ሳይጨፈለቅ መታወስ የሚች
ልበት ራሱን የቻለ አንድ ንዑስ መክፈ
ያ ይኖረዋል ስለዚህም ደራሲው አንድ
ን ሁኔታ ወይም ድርጊት አንድን ዕው
ነት ወይም ቦታ ወይም የተፈጥሮን ው
በት (ወዘተ) በሚገልጥበት ጊዜ እንደ
ቅደም ተከተሉ ለያንዳንዱ ክፍል ተዛ
ማጅ የሆኑትን ቃላትና ማስረጃዎች ያ
ከማቻል የአንዱን ክፍል ተዛማጅ ሐሳ
ብ ለሌላው ማወራረስ አይኖርበትም ።

የብዙ ዐረፍተ ነገር ድምር አንድን አ
ሳብ በሚገልጥበት ጊዜ ከፍ ብሎ በተገ
ለጠው መሠረት በአንቀጽ የሚከፋፈል
ሆኖ አንድ ራስን የቻለ ማዕከል ይፈጥ
ራል ። አንድ መክፈያ በርከት ያሉ ፓራ
ግራፎች ሊኖሩት ይችላል ።

2/ ቅደም ተከተል፡ደራሲ አንባቢው
ን ከአንዱ ሐሳብ ወደሌላ ሐሳብ ለማሸ
ጋገር የሚያስችለውን ቅደም ተከተል
በየደረጃው በትክክል ማስቀመጥ አለ
በት ። ይህም በሚሆን ጊዜ ከአንድ ከገ
ጽ 68-74 በተገለጠው መሠረት የትክ
ክለኛ ሐሳብ ሕግና ቅርጽ የመስጠት ሳ
ይንስ የሆነው ሎጂካዊ አቀማመጥ በት
ክክል መጠበቁን ማረጋገጥ የደራሲ ሁ
ሉ ተቀዳሚ ዓላማ መሆን አለበት ።

ቄስ መክብብ አጥናው



www.ethiopianorthodox.org

## ሰላም

ከገጽ ፳፪ የዞረ

ይገኛል የሚለውን እንጂ በዚህ አገር ሰላም ሰፍኖ ሕዝቡም ተስማምቶ ይኖራል የሚል አይሰማም በጠቅላላ ስለ ሰላም የሚያቀርበው ዜና እጅግም ነው ።

በዚህ ባለንበት ዓለም በጣም ከሚያሳዝነውና ከሚያስገርመው ነገር የሰው ልጆች የሚድኑበትንና ሰላም የሚመሠርቱበትን ትተው የሚጠፉበትንና ከሰላም የሚርቁበትን መርጠው መገኘታቸው ነው ።

ሰላም ከዓለም ሲጠፋ በየሀገሩ ረሀብ ጦርነት በሽታ እንደሚዛመቱና የሰው ልጅ ነቀርሳ የሆነው ድንቁርናም በመላው ዓለም እንደሚስፋፋ ሲያውቁ እነ ዚህን የመሳሰሉትን ነገሮች በማጥፋት ፋንታ ሴቶች ያለባል ቁመው እንዲኖሩ የተወለዱ ሕፃናትም ያለ እናት ያለ አባት እንዲቀሩ በተለያዩ መርዘኛ መሳሪያዎች ዓለሙን መመረዛቸው እጅግ የሚያሳዝን ነው መቸም ሰው ሁኖ ሰላምን የሚመኙ ሰላምን የሚናፍቁ የም ዕራባውያን ሥልጣኔ ያልፈነጠቀባቸው ና ኃያላኑ ከደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ያልደረሱ ናቸው ።

የሚመለከተውና የሚያነበው አልተገኘም እንጂ የሰላም መንገድማ በሰፊው ተነግሮ አልነበረምን የሰላም ባለቤት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን በሚያስተምርበት ወቅት«ሌሎችለእናንተ ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም ለሌሎች አድርጉላቸው ሌሎች በእናንተ ላይ ሊያደርጉባችሁ የማትፈልጉትን ደግሞ እናንተም በሌሎች ላይ አታድርጉባቸው» ብሏል ። ማቴ፯፡፲፪።

እንግዲህ ላስተዋለውና በቅን ልቡና ለተመለከተው ከዚህ የበለጠ የሰላም መንገድ ከዚህም የተሻለ ፍቅር ሌላ አይገኝም ። የሰው ልጆች ግን ይህንን ቀና የሆነውን በማጣመምና ወደ ጎን በመተው በፍቅር ከመኖር በጥላቻ መኖርን ይመርጣሉ ከሰላምም ጠብ ክርክርን ይሻሉ በተለይ የጥበብ ብልጭታ የፈነጠቀባቸው አንዳንድ ሰዎች ከእነሱ በስተቀር በዓለም ውስጥ ሌላ እንዳይኖርና የሰውን ከቡርነት ከምንም ሳይቆጥሩ የሰውን ዘር ከገጸ ምድር የሚያጠፋውን እንጂ ሰው የሚድንበትን ጎዳና ባለ መገንዘባቸው እንሆ ዓለሙን ሁሉ በጥርጥር ላይ ጥለውት ይገኛሉ ይህ ሁሉ ሰላምን አለመሻት መሆኑ በቂ ምስክር ነው

ነቢዩ ኤርምያስም ይህንን አስመልክቶ ሲናገር ሰላም ሰላም ይላሉ ግን ሰላም የለም»ብሏል።ኤርምያስ ፰፡፲፪ ።ነቢዩ ኤርምያስ እንደተናገረው በቃሉ ሰላም የማይል አንድም አይገኝም ችግሩ ግን በአፍ የሚነበበው ሰላም በተግባር ሲተረጐም አለመታየቱ ነው ።

ታዲያ የዚህ ዓይነቱ ሰላምታ ከልብ የመነጨ ሳይሆን ከአንገት በላይ ሰላም ሰላም ማለት ከይሁዳ ሰላምታ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ስለዚህ በዓለሙ ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን ሰው ከሰው ጋር በፍቅር እንዲኖር መጸለይና ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ማመልከት ያስፈልጋል ስለ ሰላምና ስለ ዓለም ጸጥታም መጸለይ እንደሚገባ ሲያስረዳ ነቢዩ ኤርምያስ ወደ ባቢሎን ለተማረኩት እስራኤላውያን ሰላም ይሆንላችሁ ዘንድ ወደ እርስዋ (ወደ ባቢሎን) ላስማረክኋችሁ ከተማ ሰላምን ፈልጉ ስለ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ብሏል ። ኤር.፳፱-፰ ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ«ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ (ያዙ) ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ (ያለ ሰላም ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» ብሏል ዕብ.፲፪፡፲፬ ።

ስለዚህ ይህንን መሠረት አድርገን ሰላምን እንያዝ ሰላም የደኅንነት ፍጻሜ ነውና ።

ከነፈርግብ ማርቆስ

## ትምህርተ ግዕዝ

ትምህርት ዐሥርቱ ወአርባዕቱ (፲፬)

መበእ፦ ሰላም ለክሙ አንባብያን ናሁ ንዌጥን ትምህርተ ግዕዝ ። አንትሙኒ ተደለው ለአንብቦ ። ወአስተዳልው ለውሃ ወብርዐ ለጽሒፍ ዮም እሁበክሙ ፈተና ተደለው እንከ

ቀዳማይ ፦ ተርጉሙ (ተርጉማ) ኀበ ልሳን አምሐራዊ

፩. መኑ ውእቱ ዝንቱ

፪. ዝንቱ ውእቱ አቡየ

፫. ምንት ውእቱ ዘሀሎ ውስተ እዴከ

፬. ብርዕ ውእቱ ዘሀሎ ውስተ እዴየ

፭. አይቱ ውእቱ ብሔርከ

፮. ብሔርየ ውእቱ ኢትዮጵያ

፯. ዕሩይ ውእቱ ኩሉ በመንግሥተ ኢትዮጵያ

ካልእይ ፦ ተሰጠው /ተሰጠዊ/ ዘይተሉ ተሰአሉ

## የግዕዝ ትምህርት

፰. ምንት ውእቱ ሕድረ ኢትዮጵያ

፱. ምንት ውእቱ ቀዳማዊ ልሳነ ኢትዮጵያ

፲. ዘመኑ ውእቱ መሬት በመንግሥተ ኢትዮጵያ

፲፩. እም አይቴ መጸእከ እኁየ

ሣልስይ ፦ ተርጉም ተርጉሚ ኀበግእዝ

፲፪. ሀገሬ ሩቅ ነው

፲፫. እኔ በወንበር ላይ ተቀመጥሁ

፲፬. መሬት ለአራሹ ነው

፲፭. አራሽ በዐለ መሬት ነው

፲፮. ይህ መጽሐፍ የእኔ ነው

፲፯. ያ ቤት ለመንግሥት ሆነ

፲፰. ወንበዴው ተገደለ

፲፱. ወንድሜ ከእኔ ጋር ነው

፳. ዮሐንስ እንደ እኛ መምህር ነው



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org